ኪዳነ ምሕረት

ቁጥር 26



<u>ኪዳነ ምሕረት</u>፡- የምሕረት ውል ወይም ስምምነት ማለት ነው፡፡ በጎጢአት ምክንያት ከእግዚአብሔር ተለይቶ ለነበረው ለሰው ልጅ የምሕረት ኪዳን የሆነለት በክርስቶስ ኢየሱስ ሞት (በመስቀል ላይ ሥራው) በመሆኑ ኪዳነ ምሕረት የሚለው ስም የሚገባው ለጌታችን ለኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ ነው፡፡

ማውጫ

ቀዳሚ ነገር 3

የተጨመሩ 5

የተለወጡ 12

የጎደሉ 18

ጉርሻ፤ ተጠመቀ ስለሚባለው «ሰይጣን» 23

ማጠቃለያ 29

ዋቢ 30

ኪዳነ ምሕረት

በ«ማኅበረ እስጢፋኖስ - ኢትዮጵያዊ» የሥነ ጽሑፍ አገልግሎት የሚታተም መንፈሳዊ መልእክት ነው::

አዘጋጅ፤ ቴዎድሮስ ደመላሽ

+ 251 94 66 57 513

29783 - ዐዲስ አበባ፤ ኢትዮጵያ

facebook: www.facebook.com/tewoderodemelash

Email: tewoderosdemelash@gmail.com

ቀዳሚ ነገር

«መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ‹ገድል› የሚለውን ቃል ‹ትግል፣ ፈተና፣ ውጊያ፣ ሰልፍ፣ ድልና አክሊል እስኪገኝ ድረስ የሚደክሙት ድካም፣ የሚሠሩት ሥራ፣ የሚቀበሉት መከራ› በሚል ያስቀመጠው ሲሆን፤[1] ‹ሐዋርያት፣ ሰማዕታት፣ ጻድቃን ስለ ክርስቶስ ስም ስቃዩን ሳይሰቀቁ፣ ልዩ ልዩ መከራን ታግሦ በመጋደል መከራን መቀበል ገድል ይባላል› የሚለው ከሣቴ ብርሃን ተሰማ ዐማርኛ መዝገበ ቃላት ደግሞ ‹ገድለ ቅዱሳን› የሚለውን ሲተረጉም ‹ቅዱሳን፣ ሰማዕታት ስለ ክርስቶስ ሃይማኖት ከከሃድያን ነገሥታት አደባባይ የሚሰቃዩትን ልዩ ልዩ ስቃይን የሚነግር ገድል መጽሐፍ ይባላል› ይላል።[2]

በሌላ በኩል ደግሞ « ‹የገድል ዓይነቱ ብዙ ነው› የሚለው መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት ከእነርሱም መካከል የሚከተለውን ያስነብባል፤ ‹ሥጋን ለነፍስ ማስገዛትና ማድከም ነው። ‹እንስኪ ከመዝ እትጋደል ወእትባደር ወአጠውቃ ለነፍስየ ወአገርሮ ለሥጋየ› ይላል - ነኛ ቆሮንቶስ 9፥27። እነዚህም ጾም፣ ጸሎት፣ ስግደት ሲሆኑ በራስ ፈቃድ የሚፈጸሙ ገድሎች ናቸው። ከእነዚህም ሌላ ፈጣሪያቸሁን ካዱ ለጣዖት ስገዱ እያሉ የሚያስገድዱ ዓላውያን ነገሥታት እውነተኛውን ሃይማኖት የሚያስክዱ መናፍቃን ቢነሡ ፈጣሪያችንን አንክድም ለጣዖት አንሰግድም የመናፍቃኑን ትምህርት አንከተልም በማለት ዐውቀው የሚቀበሉት ልዩ ልዩ ጸዋትው መከራ ሁሉ ገድል ይባላል›[3]»።

እንዲህ ያሉትን ታሪኮች ይዘዋል ተብለው ከሚታመኑት መካከል አንዱ ‹ገድለ ተክለ ሃይማኖት› ነው። ይህ የገድል መጽሐፍ በቤተ ክርስቲያን ብዙ ሲያነጋግር የነበረ መጽሐፍ መሆኑ ብቻም ሳይሆን አሁንም አጀንዳ ከመሆን ያልተለየ መጽሐፍ ነው። ይህ ጉዳይ ያሳሰበው ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ለሁሉ መልስ ይሰጥለት ዘንድ ተስፋ አደርጎ ያዘጋጀውና ‹ኢትዮጵያዊው ሱራፊ› በሚል ርዕስ ለንባብ ያበቃው መጽሐፍ የአሁኑ የኪዳነ ምሕረት እትም ትኩረት ሆኗል። ለዚህም ደግሞ ምክንያቱ ዳንኤል በመጽሐፉ ውስጥ ከዚህ ቀደም ሲታመኑ ከነበሩ ነገሮች በተለየ መንገድ ልዩ ልዩ ነገሮችን ያስነበበ በመሆኑ ነው።

በዳንኤል መጽሐፍ ከተነበቡት እንግዳ ነገሮች አንዱ ስለ ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥትና ስለ ክብረ ነገሥት የተጻፈው ነው። ምንም እንኳን ክብረ ነገሥት የዚህ ጽሑፍ ዋና ሐሳብ ባይሆንም ከዳንኤል ጽሑፎች ጥቂት[4] ነገሮችን በማንሣት ማቅረቡ ተገቢ ይሆናል።

በዳንኤል እምነት መሠረት፤ « ‹ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት› - በኢትዮጵያ ከዐሥራ ሦስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ የተቀነቀነ ሐሳብ ነው። ዋና መነሻው ደግሞ በንጉሥ ላሊበላ ዘመን በንቡረ ዕድ ይስሐቅ የተዘጋጀው ክብረ ነገሥት ነው» (ገጽ 23)።

---

[1] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ) መጽሐፈ ሰዋስው ወመዝገበ ቃላት ዐዲስ (1948) ገጽ 301። ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ተርጓሚ)፣ ገድለ አዳም (2002) ገጽ 2።

[2] ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፣ ከሣቴ ብርሃን ተሰማ ዐማርኛ መዝገበ ቃላት (2005 - ሦስተኛ ዕትም) ገጽ 1195። የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ ኣማርኛ መዝገበ ቃላት (ዐዲስ አበባ፣ 1993) ገጽ 509።

[3] ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት (ዐዲስ አበባ፣ 1988) ገጽ 121።

[4] ዳንኤል ሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥትን እና ክብረ ነገሥትን በተመለከተ ሐሳብ አስተያየቱን ያሰፈረው በዚህ ቡክሌት ላይ የተጻፈውን ብቻ ሳይሆን ከዚህም የሰፋ ሐሳብ ነው ያቀረበው። ሁሉን ማስፈሩና የእርሱን ሐሳብ ተንተርሶ አስተያየት መስጠቱ ገጹን ከታሰበው በላይ የሚያደረገው በመሆኑ ለማሳያ የሚሆን ነገር ማቅረቡ ላይ ብቻ ትኩረት ተደርጓል።

ሰለሞናዊ የሚባለው ሥርወ መንግሥት ከዐሥራ ሦስተኛው ክፍለ ዘመን ጅምሮ የተቀነቀነ ከሆነ ከብረ ነገሥት «ለምን ዓላማ ተጻፈ?» የሚል ጥያቄ ቢነሣ ዳንኤል የሚከተለውን መልስ ይሰጣል፤

> … ለዐዲሱ የይኩኖ አምላክ ሥርወ መንግሥት ታሪካዊ፣ ሃይማኖታዊ መደላድል መፍጠር… የዐረብ ምንጮችን መሠረት አደርጎ በቃላዊ መረጃዎችና በተራረፉ የጸሑፍ መዛግብት ላይ ተንተርሶ የተዘጋጀ አገራዊ መጽሐፍ ነው፡፡… ሁለተኛው ዓላማው ለኢትዮጵያ ነገሥታት የማንነት መሠረት መስጠት ነው፡፡ ንግሥናን ከእስራኤል ዘር በሚገኝ የዘር ተዋርዶ ብቻ እንዲሆን የሕግ መሠረት አስቀመጠ፡፡ ‹ሰለሞናዊ› የሚለውም ሐሳብ በሚገባ ጎልቶ ወጣ፡፡ ይኩኖ አምላክም የሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥት መላሽ ተባለ፡፡… ንቡረ ዕድ ይስሐቅና የዘመኑ ሊቃውንት ከብረ ነገሥትን የተረጎሙበት አንዱ ምክንያት ለኢትዮጵያ ዐዲስ ማንነትን ለመስጠት ነው፡፡ ያኾኖዋ እስራኤል ፈረሳለች፣ ክርስትናንም አልተቀበለችም፡፡ በመሆኑም ኢትዮጵያ ዐዲሲ እስራኤል ናት፡፡ በመሆኑም ለእስራኤል የተሰጠው ቃል ኪዳን ለኢትዮጵያ ተላልፏል፣ ይህም በሰሎሞንና በንግሥት ሳባ በኩል ተፈጽሟል፡፡ የቃል ኪዳኑ ታቦትም በኢትዮጵያ ነው፡፡ ስለዚህ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ጽዮን ናት የሚለውን ለመመሥረት ነው (ገጽ 25 እና 302 የግርጌ ማስታወሻ 804 እና 325 - አጽንዖት የግል)፡፡

የሚል ምላሽ ይሰጣል፡፡

ይህንና ሌሎችንም ነገሮች መነሻ በማድረግ «የሄደም የተመለሰም ሰለሞናዊ መንግሥት የለም፡፡… ከእስራኤል ዘር ጋር ማገናኘት የሕዝባችን ባህል መሆኑን የምናየው በታሪክ ነገሥታቱ ብቻ ሳይሆን በገድለ ቅዱሳኑም ይህንኑ ባህል ማገኘታችን ነው፡፡ በባህላዊው የዘር ቈጠራ ውስጥም አለ፡፡ ስለዚህም ነገሥታቱን ‹ሰለሞናዊ› የሆነና ያልሆነ ብሎ መከፋፈሉ አዋጪ አይደለም» የሚል ድምዳሜ ይሠራል (ገጽ 27 - አጽንዖት የግል)፡፡

ቀደም ሲል እንደተባለው የዚህ ጽሑፍ ዓላማ ስለ ከብረ ነገሥትም ሆነ ስለ ሰለሞናዊ ሥርወ መንግሥት ማስነበብ ባለመሆኑ ይህን ነጥብ በዚህ እናብቃና ወደ ቀጣዩ ነጥብ እንሂድ፡፡

ዳንኤል፤ ሃያ ስድስት ገድለ ተክለ ሃይማኖትን እንዲሁም ሰንክሳርን፣ ድርሳናትን፣ ሌሎች ገድሎች ያላቸውን፣ ልደተ አበውን፣ የጸሎት መጻሕፍትን፣ ታሪክ ነገሥቶችን፣ ዜና መዋዕሎችን፣ ዜና ደብረ ሊባኖስን፣ ዜና ምጽአታ ለታቦተ ማርያምን፣ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ የውጭ ሰዎችን ዘገባ፣ የቃል መረጃዎችን፣ የግብፅ ቤተ ክርስቲያንን መረጃዎችና ሥዕሎችን በመመርመር ስለ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አገኘሁት የሚለውን ለማካፈል ሞክሯል፡፡

የመጽሐፉን ዝግጅት በተመለከተ 10 ዓመታት መፍጀቱን ባይገለጽም ብዙ የተደከመበት መሆኑን ሥራው ራሱ ይናገራል፡፡ በብዙ ጥረት ከተሠራውና በምዕራፍ ሁለት ላይ ከሰፈሩትና ከላይ ከተዘረዘሩት ውስጥ በመጀመሪያ ያሰፈረውንና «ገድላተ ተክለ ሃይማኖት» በሚል ርዕሰ ስር ያሰፈረውን መሠረተ በማድረግ በገድሎች የማናምንበትን ምክንያት እናቀርባለን፡፡

የዳንኤልን ሐሳብ በጥንቃቄ ለመገልበጥ ጥረት ተደርጓል፤ ትኩረት እንዲደረግበት የሚፈለገው ክፍል ከስሩ ጎላ ያለ መስመር ተደርጎበታል፡፡ አንብበው የሚጠቀሙበት እንዲሆን ጸሎታችን ነው!!!

የተጨመሩ

ገድሎች በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ፣ ቅዱሱን መጽሐፍ መሠረት በማድረግ የሚዘጋጁ እንደ ሆኑ ይታመናል።[5] በመንፈስ ቅዱስ ረዳትነት ከተጻፉና ቅዱሱን መጽሐፍ መሠረት ካደረጉ እንደ ሌላው መጽሐፍ ዐዲስ መረጃ ተገኘ ተብሎ የማይጨመርባቸው (መረጃ ሁሉ የእሱ የሆነ ጌታ መንፈስ ቅዱስ የወደደውና እንዲጻፍ የፈቀደው ነውና የተጻፈው) መሆን አለባቸው።

ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ጋር በተያያዘ ዳንኤል ክብረት በሠራው ሥራ ውስጥ ገድለ ተክለ ሃይማኖትን መሠረት በማድረግ ይፋ ያደረጋቸውና ከዚህ በታች የሰፈሩትን ነገሮች በማየት፤ አንዱ ገድል ላይ ብቻ እንዲህ የተጨማመረ ነገር ከተገኘ ሌሎቹም ቢፈተሹስ? የሚል ጥያቄ ማንሣቱ አግባብ ይሆናል።

1

የተጨማመሩ ነገሮችን በተመለከተ ዳንኤል በመጀመሪያ ያቀረበው ሐሙስና እና እሑድ እባብ ለሚገድል ሰው ይሰጠዋል ስለተባለው ቃል ኪዳን ነው። ይህን ቃል ኪዳን በተመለከተ ብዙ የተጻፈበትና ቤተ ክርስቲያንንም በብዙ ያስተቸ መሆኑ ይታወቃል። ከዚህም የተነሣ ሲሰጡ ከነበሩት አስተያየቶች መካከል «እባብ» የተባለው አማናዊውን እባብ ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ በእባብና በዘንዶ የተመሰለውን ጠላታችንን ሰይጣንን ነው የሚለው ይገኝበታል።

ገድሉ በእነዚህ ቀናት እባብ መገደል የሚያስገኘውን በረከት «... በዚህ ቦታ ላይ ዐቀም የለውም። እሑድና ሐሙስ ቀን <u>እባብ የገደለ</u> የክርስቲያን ወገን ሁሉ <u>ኀጢአቱ ይሰረይለታል</u> ብለህ ለልጆችህ ንገራቸው ብሎ ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ የነገረኝን አሁንም እነግራችኋለሁ በልባችሁ ጠብቁት»[6] በማለት በግልጽ ያስቀመጠ በመሆኑ ማስተባበሉ ትንሽ አስቸጋሪ ሳያደርገው አልቀረም። በመሆኑም ዳንኤል ክብረት፤

> ...የመጀመሪያዎቹ ቅጅዎች ታሪካዊ መረጃውን በዝርዝር ሲያስቀምጡት የኋለኞቹ ግን ጠቅለል ያደርጉታል። ምናልባት ግን ጸሐፊው <u>የእጨጌ ዮሐንስ ከማን ቅጅ ተጠቅሞ መግቢያ አክሎ የጻፈው መሆን አለበት</u>። የእጅ ጽሑፉ የዐሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መሆኑን ያመለክታል። በውስጥ ሐሙስና እሑድ እባብ ለገደለ ሰው የተሰጠውን ቃል ኪዳን ስንመለከት ግን <u>የእጨጌ ዮሐንስ ከማን ቅጅ[7] ይዞ ተጨማሪ ቃላዊ መረጃዎችን አክሎ የተዘጋጀ መሆን አለበት</u>። ነገር ግን ቅጅው ከጣና ቂርቆሱ ቅጅ ይቀድማል። አተራረኩ በቀጥታ የእጨጌ ዮሐንስ ከማን ቅጅ ስለሚከተል ገድሉ ከእጨጌ ዮሐንስ ከማ

[5] ገድለ ተክለ ሃይማኖት (ነሐሴ 1989) መግቢያውን ይመልከቱ።

[6] ገድለ ተክለ ሃይማኖት (ነሐሴ 1989) ገጽ 186።

[7] ገድለ ተክለ ሃይማኖትን ለመጀመሪያ ጊዜ እንደጻፈው የሚታመነው እጨጌ ዮሐንስ ከማ የተባለና ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት በኋላ ሰባተኛው የደብረ ሊባኖስ እጨጌ ሆኖ በተሾመ ሰው ነው (ኢትዮጵያዊው ሱራፊ ገጽ 76)። በእርግጥ በዚህ ሰው እጅ ተጽፏል የሚባለው ገድለ ተክለ ሃይማኖት ብቻ ሳይሆን ሌሎችም ገድላት ናቸው።

ቅጅ ተገልበጦ ነገር ግን ዳብሮ እዚያው ዳጋ የተጻፈ ነው (ገጽ 82 - አጽንዖት የግል)፡፡...

ለዚህ ደግሞ ምክንያት ብሎ ያስቀመጠው፤ «በዚያ የግራራይ በረሐ ለሚኖሩ መነኮሳት ትልቁ ችግር እባብና ዘንዶ ስለሆነ እነርሱን ለማበረታታት የተሰጠ ቃል ነው፡፡ ሐሙስና እሑድ ለምን እንደተመረጠ ግን ግልጽ አይደለም፡፡ ምናልባት የመነኮሳቱ የእረፍት ጊዜያት ይሆናሉ» የሚለውን መሆኑ ቀደም ሲል ለእዚህ ቃል ኪዳን እንደማብራሪያ ሆነው ሲቀርቡ የነበሩት ነገሮችን ውሃ እንዲባለው አደርጓል (ገጽ 85 - አጽንዖት የግል)፡፡ ይህ ማለት ደግሞ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው የነገረኝ በማለት የተናገሩት ነው የተባለውና በኋላ ዘመን የተጨመረው ሐሳብ ውሸት ነው ማለት፡፡ ከዚህም ሌላ ጎጢአቱ ይሰረይለታል የተባለውም ቃል ኪዳን (የተሰፋ ቃል) ባዶ ቃል በመሆኑ እባብ ለመግደል በሚል በእባብ ሲነደፍ የነበረው ሁሉ ከንቱ ነው ማለት ነው፡፡

2

ከእባቦች ገደላ ስንወጣ «የዳጋው ቅጅ የእጨጌ ዮሐንስ ቅጅ ቀጥተኛ ገልባጭ አይደለም፡፡ የገድሉ ጸሐፊ የቅዱሱን ታሪክ ከእጨጌ ዮሐንስ ከማ ቅጅ ወስዶ ታሪክና ማብራሪያ ጨምሮበታል፡፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማብራሪያም ያክላል፡፡ ከገድሉ በቀር ተአምራት በውስጡ አልያዘም» የሚለውን እናገኛለን (ገጽ 86 - አጽንዖት የግል)፡፡

በዚህ የገድል ቅጂ ላይ እንደሚታየው ማብራሪያ ብቻ ሳይሆን የታሪክ ጭማሪም አለ፡፡ ለተሠራው ጭማሪ ምንጩ ምን እንደሆነ፣ መጨመር ለምን እንዳስፈለገና ጭማሪው ምን ያህል አስተማማኝ እንደ ሆነ ማረጋገጫ ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡

3

በገድሎቹ[8] ውስጥ የሚገኙት ጭማሪዎች እነዚህ ብቻ አይደሉም፡፡ ዐጽመ ታሪክ ብቻ በመውሰድና የራሱን ጭማሪ በማከል ስለተጻፈው ገድል ዳንኤል የሚከተለውን ያስነብባል፤ «የጣና ቂርቆሱ ገድል ጸሐፊ ከእጨጌ ዮሐንስ ከማ ቅጅ መሠረቱንና ዐጽመ ታሪኩን ቢይዝም ከቃል መረጃዎች እንደገና እየወሰደ ጨምሮበታል» (ገጽ 90 - አጽንዖት የግል)፡፡ በዚህም የገድል ቅጂ ላይ ማሻሻያ ሲሠራና «መሠረት» የተባለውን ሲለቅ ይታያል፡፡

4

ከዚህም በተጨማሪ ደግሞ «ይህንን መሰሉ ትረካ በኋላ ዘመን የደቀ መዛሙርቱ ስም ከታወቀ በኋላ የተጨመረ ሳይሆን አይቀርም፡፡ እንደ እኔ የሐይቁ ከዋልድባው በኋላ የተጻፈ ወይም ከሌላ ዐዳዲስ መረጃዎች የተጨመሩበት ሳይሆን አይቀርም» በማለት ዳንኤል ጥርጣሬውን ያስነብባል (ገጽ 106 - አጽንዖት የግል)፡፡ ከጥርጣሬ ወጥቶ ገድሎች ከእውነት የራቀ ሐሳብም በውስጣቸው መሸሸጋቸውን ጭምር እንዲህ ያስነብባል፤

[8] «ገድሎቹ» በሚል በብዙ ቍጥር የተቀመጡት ልዩ ልዩ ገድሎችን በተመለከተ ሳይሆን አንዱን ገድለ ተክለ ሃይማኖት በተለያዩ ቅጅዎች ለማመለከት ተብሎ ነው፡፡

ለ12 ዓመ[ታ]ት በደብረ ዳሞ ካገለገሉ በኋላ የትግራይ ገዳማትን ጎበኙ። ከደብረ ዳሞ ሲወርዱ ሐብሉ ተበጥሶ በክንፍ ከመሬት ማረፋቸውና ሰባት ክንፍ ማግኘታቸው ተተርኳል። <u>እስከ አሁን ያገኘናቸው ገድሎች[9] ይሄንን አይተርኩልንም</u>። ከሁለተኛው የደብረ ሊባኖስ ቅጅ በቀር። የሚጣመቁም ከዚያ የወሰደወ ይመስላል። *መጀመሪያ* ወደ ዋሊ ገዳም፣ ከዚያም ወደ ገዳመ ሐውዜን፣ ቀጥሎም ወደ ገዳመ ዳጌ ከዚያም ወደ ኢየሩሳሌም አመሩ። በዚህ ገድል ላይ ሁለት ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዘዋል። <u>የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢየሩሳሌም ጉዞ በኋለኞቹ ቅጅዎች ብቻ የሚገኝ ታሪክ ነው</u>። ከዚህ የተነሣ አንዳንድ ሊቃውንት <u>የኋላ ጭማሪ እንጂ ቅዱሱ ከኢትዮጵያ አልወጡም</u> ይላሉ (ገጽ 112 - አጽንዖት የግል)።

የሚል ሐሳብ ያስቀመጠው ዳንኤል፤ በዚህ ሐሳቡ ደግሞ አንዳንድ ሊቃውንት ያላቸውን ተገን በማድረግ በየገድሉ ውስጥ ውሸት እንኳ ሊቀመጥ እንደሚችል አሳይቶናል። ምክንያቱም አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከኢትዮጵያ ወጥተው ባያውቁም በገድሉ ላይ እንደሚታየው ግን ሁለት ጊዜ ከኢትዮጵያ ወጡ ተብሎ ሰፍሯል። ታዲያ እንዴት በገድሎች ለማመን ይቻላል?

5

ከዚሁ ከኢየሩሳሌም ጉዳይ ሳይወጣ ቀደም ሲል ሁለት ጊዜ ጉዞ እንዳደረጉ ገድሎቹ ያሰፈሩትን ያስነበበው ዳንኤል ‹የምን ሁለት ጊዜ ብቻ?› በሚል የሚከተለውንም አስቀምጧል፤ «ይሄኛው ገድል አቡነ ተክለ ሃይማኖት <u>ኢየሩሳሌም ሦስት ጊዜ እንደ ሄዱ ይተረካል</u>። ሁሉም ይህን ትረካ የሚከተሉ ቅጅዎች የኢየሩሳሌሙን ጊዜ[ጉዞ] አንድ ዓመት ያደርጉታል። <u>በአንድ ዓመት ሦስት ጊዜ ኢየሩሳሌም መውረድ ግን የሚቻል አይመስልም</u>» (ገጽ 135 - አጽንዖት የግል)። ይህ ማለት ደግሞ ገድሎቹ ውሸት ብቻ ሳይሆን ግነትም ይገኝባቸዋል ማለት ነው። ግነቱ ያስፈለገው ገድሎቹ ቅዱስ ናቸው የሚሏቸው አካላት ቅድስና ከፍ ለማድረግ በሚል መሆኑ ይታወቃል።

6

ገድሎች የሚጻፉት በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ መሆኑን የሚያምኑ ሰዎች አሉ። «እስትንፋስ እግዚአብሔር ናቸው» ለማለትም የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ንባባትን ያለ መልእክታቸው እስከመጥቀስ ድረስም ሄደዋል። በእርግጥ እንደሚባለው ገድሎች የሚጻፉት በመንፈስ ቅዱስ ርዳታ ነው ወይስ መረጃ በተገኘ ጊዜ ሁሉ በማዳበር? የሚል ጥያቄ የሚያጭር ሐሳብ በዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ በሚከተለው መልኩ ይገኛል፤

[9] ዳንኤል እዚህ ስፍራ ላይ «እስከ አሁን ያገኘናቸው ገድሎች» ያለው ከዚህ ቀደም ሲል 7 ገድሎችን ጠቅሶ ሐሳባቸውን አስቀምጦ ነበርና እነርሱን ለማመልከት ሊሆን ይችላል። እንደዚያ ከሆነ በዚህ ስፍራ ላይ የሰፈረው ሐሳብ በሌሎች ገድሎች (የዮሐንስ ከማን ቅጅ ጨመሮ) የሌለና እንግዳ (የተጨመረ) ሐሳብ መሆኑን ለመረዳት አያስቸግርም።

የደብረ ሊባኖስ ቅጅ የተጻፈው በ0ሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መሆኑን ብዙዎች ሊቃውንት ተሰማምተውበታል፡፡ በብዙዎች የደብረ ሊባኖስ ቅጅዎች ላይ ገድሉ የተጻፈበትን ዘመን በተመለከተ ሦስት ነገሮችን ይነግሩናል፡፡ የመጀመሪያው አስጻፊውን፣ ሁለተኛው ዘመኑን፣ ሦስተኛው ደግሞ በዘመኑ የነበረውን ንጉሥ በተመለከተ ነው፡፡ አስጻፊውን ቀደም ብለን እንዳነሣነው ለአቡነ ዮሐንስ ከማና ለአቡነ ጴጥሮስ ይሰጣሉ፡፡ አቡነ ዮሐንስ ከማን በተመለከተ መጽሐፉ በእርሱ ዘመን መገለጡን ነው የሚነግሩን፡፡ ይህም የመጀመሪያው ቅጅ በዮሐንስ ከማ ጊዜ መጻፉን ያሳየናል፡፡ <u>በኋላ ግን መረጃዎች እየተሰባሰቡና ተጓምራቱም እየበዙ ሲሄዱ ሰፊውን ዛሬ ከሞላ ጎደል የምናውቀው የደብረ ሊባኖስ ቅጅ በአቡነ ጴጥሮስ አማካይነት እንደ ገና ተጽፏል</u>፡፡... (ገጽ 117 - አጽንዖት የግል)

በዚህ በዳንኤል ሐሳብ ውስጥ እንደምናየው ገድሉን ለመጻፍ የመንፈስ ቅዱስ ርዳታ አላስፈለገም፡፡ ከዚያ ይልቅ «... መረጃዎች እየተሰባሰቡና ተጓምራቱም እየበዙ ሲሄዱ ...» ገድሉ አሁን ያለውን መልክ መያዙን ነው ማረጋገጥ የተቻለው፡፡

7

ከዚህ ባስ ሲል ደግሞ ለተነሣ ጥያቄ መልስ ለመስጠት በሚል የመጨመር መልሶ ደግሞ የማውጣት ሥራ የሚሠራ መሆኑንም የዳንኤል መጽሐፍ ያስነበበው በሚከተለው መልኩ ነው፤

በመጀመሪያ አካባቢ በተጻፉት ገድሎች ታሪኩ እንዳለ ቀርቦ ነበር፡፡ የእጨጌ ዮሐንስ ከማ የ1918 ዓመተ ምሕረት ቅጅ ይህንን ይመሰክራል፡፡ በኋላ ዘመን ደግሞ ጉዳዩን በተመለከተ ጥያቄ ተነሥቶ ነበር፡፡ <u>በዚህ ምክንያት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ታሪካዊ ማብራሪያ ታክሎበታል፡፡</u> ልክ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ያጠመቁትን ‹ሰይጣን› በተመለከተ[10] የደብረ ሊባኖሱ (የአዘዘው የ0ሥራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቅጅ) ገድል **<u>እጅግ ሰፊ ማብራሪያ</u>** እንደሰጠው ማለት ነው፡፡ <u>በሦስተኛ ደረጃ በተጻፉት ቅጅዎች ግን ታሪኩ **<u>ፈጽሞ</u>** እንዲወጣ ተደርጓል</u>፡፡ በደብረ ሊባኖሱ ገድል ላይ አለመኖሩና የሚጣቁና የወይንጌውን ለመሠረዝ[11] የተደረገው ሙከራ ይህን ይነግረናል (ገጽ 125 - አጽንዖት የግል)፡፡

ጥያቄ ሲነሣ ለጥያቄው መልስ ለመስጠት መነሣት አግባብ ነው፡፡ መልስ የሚሰጠው ግን የገድሉ አካል ለማሰመሰል «እጅግ ሰፊ ማብራሪያ» ገድሉ ውስጥ እየጨመሩ ሳይሆን በተለየ መንገድ መሆን ነበረበት፡፡ ለምሳሌ በዘመናት ሁሉ ጥያቄ የሚነሣበት መጽሐፍ አለን፤ መጽሐፍ ቅዱስ፡፡ በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ለተነሡት ጥያቄዎችም ሆነ ለቀረቡት ትችቶች አግባብ ነው የሚሉትን ምላሾች አቅርበዋል፡፡

---

[10] ይህን ‹ሰይጣን› በተመለከተ ዳንኤል እንዴት ባለ ጥበብ ለማለፍ እንደሞከረና ሌሎች ነጥቦችንም በዚህ ጽሑፍ «ጉርሻ፤ ተጠመቀ ስለሚባለው ‹ሰይጣን› » በሚል ርዕስ ስር የቀረበውን ጽሑፍ መመልከቱ ጠቃሚ ነው፡፡

[11] ስለ መሠረዝ የጻፈውን በተመለከተ በዚህ ጽሑፍ «የጎደሉ» በሚል ርዕስ ስር የሰፈረው ላይ ሰፋ ያለ ነገር ቀርቧልና እሱን መመልከት ይቻላል፡፡

እነዚህ ምላሾች የቀረቡት ግን የመጽሐፍ ቅዱስ አካል በመሆን ሳይሆን ራሳቸውን ችለው ነው፡፡ ገድሎችም «እስትፋሰ እግዚአብሔር» እንደ ሆኑ ከታመነ መንፈስ ቅዱስ ይሁን ብሎ ያስጻፈውን ብቻ ጠብቆ ለትውልድ ለማስተላለፍ ከመትጋት ይልቅ የወደደ እየተነሣ የሚጨምርባቸው መሆኑ በገድሎች «ቅዱስ» መጽሐፍነት ላይ ጥያቄ ያስነሣል፡፡

8

ሰዎቻችን ገድሎችን ጥያቄ ለመመለስ ብቻ ሳይሆን ታሪክን እንደ ወደዱ ለመቃኘትም እንደሚጠቀሙበት በዳንኤል መጽሐፍ ውስጥ የሚታይ ነገር ነው፤

> የደብረ ሊባኖሱ ሁለቱም ቅጅዎች ይኩኖ አምላክ የነገሠው ፍስሐ ጽዮን[12] ቅስና በተቀበለበት ዓመት መሆኑን ይነግሩናል፡፡ ወላጆቹ ያረፉትም (ነሐሴ 12 እና 17 ቀን) ቅስና ከመቀበሉ በፊት መሆኑን ሁለተኛው ቅጅ ይገልጣል፡፡ ያ ከሆነ ደግሞ ክህነት የተቀበለው በ1260 ዓመተ ምሕረት ይኩኖ አምላክ በነገሠበት ዘመን ነው ማለት ነው፡፡ ይኩኖ አምላክ በነገሠ በወሩ ነው ወላጆቹ ያረፉት፡፡ የገድሉ ቅጅ ይኩኖ አምላክ የነገሠው በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘመነ ስብከት ሐምሌ 7 ቀን ነው ይላል፡፡ ራሱ ገድሉ እንደሚነግረን ግን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ስብከት የጀመሩት ይኩኖ አምላክ ከነገሡና ወላጆቻቸውም ካረፉ በኋላ ነው፡፡ <u>በመሆኑም ይሄ ሐሳብ የኋላ ጭማሪ መሆን አለበት</u>፡፡... በ1508 ዓመተ ምሕረት የተጻፈው ሁለተኛው የደብረ ሊባኖስ ቅጅ ስለ ይኩኖ አምላክ መንግሥትን መመለስ ሲተርክ ‹በጸሎቱ አቡነ ተክለ ሃይማኖት› የሚል አለው፡፡ <u>ይሄ ደግሞ በመጀሪያውና በ1418 ዓመተ ምሕረት በተጻፈው ላይ የለም</u>፡፡... አንዳንድ መዛግብት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ይኩኖ አምላክን ያነገሡት በሐይቅ 12 ዓመት ከቆዩ በኋላ ነው ይላሉ፡፡ ይሄ ከሆነ ደግሞ ይኩኖ አምላክ ከነገሠ ከ32 ዓመታት በኋላ ይሆናል፡፡ <u>የኋላ ሰዎች (በተለይ በሳንደር ዘመን ብዕለ ነገሥት ከተጻፈ በኋላ) አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ከይኩኖ አምላክ ጋር ለማገናኘት ሲሉ የጨመሩት እንጂ</u> ዐፄ ይኩኖ አምላክ ሲነግሥ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ገና በሸዋ በክህነት አገልግሎት ላይ ነበሩ፡፡... ከዚህ አንጻር ስንመለከተው፤
>
> 1. በገድለ ተክለ ሃይማኖት ውስጥ የሚገኘው የነገሥታት ዝርዝር፣
> 2. የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ለይኩኖ አምላክ የመጸለያቸውና የማንግሣቸው ጉዳይና[13]

---

[12] ፍስሐ ጽዮን የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የመጀመሪያ ስማቸው ነው፡፡

[13] ዳንኤል ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት ምክንያት ከሆኑት ውስጥ አንዱ የይኩኖ አምላክ ንግሥና ላይ መውጣት በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ድጋፍ ነው የሚለው ሐሳብ በልዩ ልዩ ጸሓፍት ለንባብ መብቃቱን በመመልከቱና በእርሱ እምነት ጸሓፍቱ የተሳሳቱ በመሆናቸው ትክክለኛ ነው የሚለውን ነገር ለማቅረብ ነው፡፡ በዚህ ስፍራ ላይም እያደረገ ያለው ያንኑ ነው፡፡ ነገር ግን በእርሱ እምነት መሠረት ተሳስተዋል የሚላቸው ሰዎች «ስሕተታቸው» እንዲሁ ነፋስ ያመጣውና መረጃ አልቦ ሳይሆን አሁን ዳንኤል በዚህ ስፍራ ላይ እንዳሳየን በመንግሥት ለወጡ ወቅት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ድርሻ እንደነበራቸው የሚያሳዩ ገድላት ናቸው፡፡ ዳንኤል እንደሚለው ግን እነዚህ ገድላት ይህን ሐሳብ የጻፉት «ለሌላ ፍላጎት» ነው፡፡ ሌላ ብሎ አድፈንፍኖ ያለፈውን ፍላጎት ግን ግልጽ ማድረግ አልፈለገም፡፡

3. ከይኩኖ አምላክ ጋር ተደረገ የሚባለው ቃል ኪዳን
<u>በኋላ ለሌላ ፍላጎት የተጨመረ ሐሳብ እንጂ ከቀደምቱ የገድሉ ቅጅዎች የማይገኝ ሐሳብ ነው</u>... (ገጽ 402 እና 403 - አጽንዖት የግል)::

ዳንኤል ሊነግረን ባልፈለገውና «ሌላ ፍላጎት» ብሎ ባለፈው ምክንያት ታሪክን የሚያዛባና ውሸት የሆነ ነገር የገባበት ገድል ባለቤት መሆናችንን በመጽሐፉ አሳውቆናል::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ደግሞ «የታሪኩ ጸሐፊ የደብረ ሊባኖስ ገዳምን ምሥረታ ወደ ዘመነ ዛጉየ ወስዶታል በአቡነ ተክለ ሃይማኖትና በይኩኖ አምላክ መካከል ቃል ኪዳን ነበር የሚለው በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጀመረውን ትረካ ይዞ ነው የመጀመሪያው የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ገድል እንደሚያሳየን ግን አቡነ ተክለ ሃይማኖትና አፄ ይኩኖ አምላክ አልተገናኙም:: ያረፉት በ1305 ዓመተ ምሕረት ነው:: ደብረ ሊባኖስ ከተመሠረተ ከ28 ዓመት በኋላ:: ያ ከሆነ ደግሞ ወደ ደብረ ሊባኖስ የመጡት በ1277 ዓመተ ምሕረት ነው:: ይኩኖ አምላክ ከማረፉ ከአንድ ዓመት በፊት:: <u>በኋላ ግን ይህ ትረካ ደብረ ሊባኖስን ከቤተ መንግሥቱ ጋር ለማስተሳሰር ሲባል ይበልጥ እየተስፋፋ መጣ</u>» የሚል ነገርም ጽፎ ይገኛል (ገጽ 898 የግርጌ ማስታወሻ ቍጥር 2731 - አጽንዖት የግል):: በዚህም ቤተ ክርስቲያን በፖለቲካ ውስጥ የነበራትን ድርሻ ብቻ ሳይሆን ለፖለቲካው ፍጆታ ሲባል ዐዳዲስ ነገሮችን በመፈጠር የ«ቅዱሳን» ታሪክ ማድረግና በገድሎች ውስጥ መክተትም ምንም ችግር የሌለ መሆኑን እንረዳለን::

9

«ይህ ቅጅ የሐይቅ እስጢፋኖስ ቅጅ ነው» የሚለው ዳንኤል ክብረት የሐይቅ ቅጅ ነው በሚለው ገድል ላይ ደግሞ፤

በገደለ አቡነ ኢየሱስ ሞአ ላይ የምናገኘው አቡነ ኢየሱስ ሞአ አስኬማን ከአባ ዮሐኒ እንዲያመጡላቸው አቡነ ተክለ ሃይማኖትን መጠየቃቸውን <u>የሚገልጠው ትረካ የለውም</u>:: እስከ አሁን ያገኘናቸው የገድለ አቡነ ኢየሱስ ሞአ ቅጅዎች ከዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ የተጻፉ ናቸው:: <u>ምናልባትም ይህ ጉደይ የኋላ ጭማሪ ሊሆን ይችላል</u>:: <u>በዳጋው ቅጅ ላይ የነበረውን **ታሪክ ደምስሶ ይህንን ታሪክ ለመጻፍ** የተደረገውን ሙከራ ስናይ፣ ይህ ነገር ትኩረት ያገኘበት ዘመን እንደ ነበረ ይጠቁመናል</u>:: ምናልባትም ዐሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሁለተኛ ኣጋማሽ ሳይሆን አይቀርም (ገጽ 568 ግርጌ ማስታወሻ ቍጥር 1669 - አጽንዖት የግል)::

በማለት የገድል ጸሓፍት እነርሱ ከፈለጉ ታሪክ እየሠረዙ ደስ ያላቸውን ሌላ (ምናልባትም የሌለ) ታሪክ ለመጻፍ የሚታዘዝ እጅ እንዳላቸው አሳይቶናል::

10

«በኋላ በመጡት ገድሎች ላይ የተጨመረ...» (ገጽ 590 እና 680 - አጽንዖት የግል) ነገር መኖሩን የሚናገረው የዳንኤል መጽሐፍ ሐሳብ ለመጨመር እንደ ምክንያት

ሆነው ከተቀመጡት ውስጥ «... በኋላ ዘመን የደብረ ሊባኖስ ተሰሚነት እየጨመረ ሲመጣ...» የሚለው ይገኝበታል።

በዚህ ደግሞ የአንደ ገዳም ተጽእኖ መፍጠር (ተሰሚነት ማግኘት) ገድሎቹን እንዳሉ ጠብቆ ከማቆየት ይልቅ፤ የወደደውን እንዲጽፍ፣ የተመቸውን እንዲጨምር በር የሚከፍት መሆኑን ያሳያል። ስለዚህ ገድሎችን በመነካካትና ቀደም ሲል ከነበሩበት ሁኔታ በተለየ መልኩ እንዲዘጋጁ የማድረጉን ሥራ የሚሠሩት ግለሰቦች አይደሉም ማለት ነው።[14]

፲፩

«ሐሙስና አሑድ እባብ የገደለ...» የሚለውን ታሪክ (ቃል ኪዳን) የተጨመረ መሆኑን የነገረን ጸሐፊው ምክንያቱንም አስቀምጦ ነበር። አሁንም በሌሎች ገድሎች ላይ የሌለና በኋላ ዘመን የተጨመረ ታሪክ (ቃል ኪዳን) አለ ይለንና ምክንያቱንም ጭምር እንዲህ ያስቀምጣል፤

> ... በሚጣቁና በመንዙ ቅጂዎች ላይ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን የመቃብር ስፍራ በቃል ኪዳን ጸንተው ላለመልቀቅ ቀደምት ገዳማውያን ያደረጉት ተጋድሎ ተጽፏል። 300 እና 400 ሰዎች በሕማመ ብድብድ እያለቁ የተረፉት በመቀጠላቸው የተነሣ ትውፊቱ ሳይቋረጥ መድረሱን ይናገራል። «ዘሞቱ በሕማመ ብድብድ እኁልቁሙ ምስለ ሰማዕታት - በሕማመ ብድብድ የሚሞቱትን ሰማዕታት እቈጥራቸዋለሁ» <u>የሚል ቃል ኪዳን ግን በቀድሞዎቹ ቅጂዎች የለም። በኋላ ዘመን በሽታው እየበረታ ሲመጣ መነኮሳቱ እንዲጸኑ የተጨመረ ነው</u>... (ገጽ 770 ግርጌ ማስታወሻ ቍጥር 2295 - አጽንዖት የግል)።

እንደ ዳንኤል እምነት መነኮሳቱ እንዲጸኑ ተብሎ የተጨመረው ይህ «ቃል ኪዳን» እስከ ዘመናችን እያገለገለ መሆኑ ብቻ ሳይሆን አንዳንዶች ጥብቅና ቆመው ሲሟገቱለት በማኅበራዊ መገናኛ ብዙኀን ይሰማል። ይህም የገድሎችን አሳሳችነት በሚገባ ያሳያል ተብሎ ተስፋ ይደረጋል።

፲፪

[14] ዳንኤልን እዚህ ጋር ማመስገን አግባብነት ሳይኖረው አይቀርም። ምክንያቱም በቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙትን አንዳንድ እንግዳ ታሪኮችና ኢ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሐሳቦችን በማንሣት ቤተ ክርስቲያን ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ትመለስ ለሚለው ጥሪ እየተመለሰ የነበረው መልስ ሐሳቡን በተሻለ መረጃና ሐሳብ መሞገት አይደለም። በተለይም በማኅበራዊ መገናኛ ብዙኀን እየተስተጋቡ ከሚገኙት ሐሳቦች ውስጥ «እነዚህ ተሃድሶዎች የቤተ ክርስቲያንን መጻሕፍት ራሳቸው በርዘውና በክለው መልሰው ደግሞ ቤተ ክርስቲያንን ይከሳሉ» የሚለው ጎልቶ ይሰማል። ዳንኤል ግን በዚህ መንገድ ስሕተቱን ለመሸፈን ከመሞከር ይልቅ የተሻለ የሚለውን ምክንያት ለማቅረብ ነው የሞከረው። ይሄውም የቤተ ክርስቲያን ሰዎች የሚባሉ ከዚያ ሲያልፈም ገዳማት ገድላትን ያሻቸውን እንደሚያደርጉ ነው ያሳየን።

በመጨረሻ በመጽሐፈ ሰዓታት[15] ውስጥ ተሠርቷል የሚለውን ጭማሪ በማቅረብና ይህን ርዕስ በመዝጋት ‹የምን መጨመር ብቻ መለወጥም ካስፈለገ የመለወጥ ሥራም ይሠራል› የሚለውን ወደምናቀርብበት ወደ ቀጣዩ ርዕስ እንሻገር፤

መጽሐፈ ሰዓታትን በተመለከተ ዳንኤል፤ «ምንም እንኳን ከዐሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ የገባ ጭማሪ ቢሆንም በሰዓታት ድርሰት ከሚነሡት አንዱ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ናቸው» በማለት ገድሎች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎችም መጻሕፍት እንደተፈለጉ ሊሆኑ እንደሚችሉ አሳይቶናል (ገጽ 182 - አጽንዖት የግል)፡፡

የተለመጡ

ገድሎች ሐሳብ ማዳበሪያ፣ ዐዳዲስ ነገር ሲገኝ መሙያ (የሚጨመርባቸው) ብቻ አይደሉም፡፡ ከዚህም ሌላ በውስጣቸው ያለው ሐሳብ ካልተወደደ በሌላ ሐሳብ ሊተኩ የሚችሉ መሆናቸውንም እንመለከታለን፡፡ ከዚህ በታች የሰፈሩትን ሐሳቦች ዳንኤል ክብረት በመጽሐፉ ውስጥ በልዩ ልዩ ቦታዎች አስነብቧል፤

1

በዚህ ነጥብ ስር በመጀመሪያ የምናገኘው «ይህ ነገር በኋላ ዘመን ለውጥ ገጥሞታል» የሚለውን ነው፡፡ ሐሳቡ በሚከተለው መልኩ ስፍሯል፤

> …እንጦንስ አስኬማውን ከመላእክት እጅ አገኘ፡፡ ይህም ቅዱስ አባት የምንኩስናን ቀንበር ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳዘዘው ከአባታችን ከበጸሎተ ሚካኤል ተቀበለ ነው የሚለው፡፡ ይሄ ነገር በኋላ ዘመን ለውጥ ገጥሞታል፡፡ የደብረ ሊባኖሱ ቅጅ ‹ወከማሁ ዝንቱ አብ ቅዱስ ነሥአ አርዐተ ምንኩስና እም እደ አቡነ ኢየሱስ ሞአ - ይህም ቅዱስ አባት የምንኩስናን ቀንበር ከአቡነ ኢየሱስ ሞአ ተቀበለ› ይላል፡፡ አባ በጸሎተ ሚካኤል በአባ ኢየሱስ ሞአ ተተክተዋል (ገጽ 78 - አጽንዖት የግል)፡፡

ይህ የሆነበት ምክንያት ግልጽ ባይሆንም አባ በጸሎተ ሚካኤል ወጥተው አቡነ ኢየሱስ ሞአ እንዲገቡ የተፈለገው በአጋጣሚ አለመሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ ውስጥ የገድሉ አዘጋጆች ማስተላልፍ የፈለጉት መልእክት አለና፡፡

2

ከዚህ በኋላ የምናገኘውና አንድ ገድል ሆኖና አንድ ታሪክ ይዞ በልዩ ልዩ ቅጂዎች ላይ የተሠራውን የተለያየ ሥራ ያሳየበትን ክፍል ነው፡፡ በዚህ ክፍል ላይ ሰፋ ያለ ነገር

[15] የአባ ጊዮርጊስ መጽሐፍ እንደ ሆነ የሚታመነው መጽሐፈ ሰዓታት ከጸሎት መጻሕፍት የሚመደብ መጽሐፍ ነው፡፡ «እስከ ዐሥራ አራተኛው ክፍለ ዘመን ድረስ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት በያሬዳዊ ዜማ ብቻ ይፈጸም ነበር፡፡ ከዚያ ወዲያ ግን ሌላ ዐዲስ ተፈጠረ፡፡ እሱም ሰዓታት የሚባለው ነው፡፡… ሰዓታትና አቋቋም ዋናው የያሬድ ዜማ እንዲዳከም ምክንያቶች ሆነውታል» (ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም፣ ክርስትና በኢትዮጵያ - ክፍል ሁለት፤ (ነሐሴ 1991) ገጽ 61፡ 93፡፡ ቴዎድሮስ ደመላሽ፣ አታስቀኑት (መጋቢት 2011) ገጽ 11 የግርጌ ማስታወሻ)፡፡

የተቀመጠ በመሆኑ ሁሉንም እዚህ ላይ ማስፈሩ ገጹን እንዲበዛ ያደርገዋልና ዳንኤል ልዩነት እያለ ያስቀመጠውን ብቻ በማስቀመጥ ማሳየቱ ነው የተሻለ ሆኖ የተገኘው፡፡

> … በሌሎች ገድሎች መሠረት አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ዳሞት የሄዱት ከዊፋት ወደ ጉራጌ ከጉራጌም ወደ ዳሞት በወታደሮች ተይዘው ነው፡፡ በዚህኛው ገድል መሠረት ግን ተማርከው ነው የሄዱት፡፡… በሌሎች ገድሎች ‹ከዚህ በፊት ማንም ያልተጠራበት› ተብሎ የቀረበው በዚህኛው ገድል ‹ዐዲስ ስም ሰጠሁህ› ነው የሚለው፡፡ ዐዲስ ስም ሰጠሁህ ማለትም ከዚህ በፊት ሌላ ሰው ያልተጠራበት ማለትን አያመጣም፡፡ ለተሰያሚው ዐዲስ ስም መሆኑን እንጂ፡፡… እንደዚህኛው ገድል ከሆነ ከከታታ በኋላ ወደ ዳሞት ተመልሰዋል፡፡ ሌሎቹ ገድሎች ግን ከዳሞት ከወጡ በኋላ እንዳልተመለሱ ይነግሩናል፡፡… በሌሎቹ ገድሎች አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለአቡነ ኢየሱስ ሞአ አስኬማውን ያመጡላቸው ከደብረ ዳሞ ነው፡፡ እዚህ ግን ራሳቸው ሰጧቸው ይላል፡፡… በሌሎች ገድሎች የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቀ መዝሙር ከአጋት ወንዝ አጠገብ አገኘው የሚሉት ‹ሰይጣን› እዚህ ታሪኩ የለም፡፡ …በሌሎቹ ገድሎች የማናገኘው አንድ ተአምር እዚህ አለ፡፡… በሌሎች ገድሎች ይህንን የጠየቀችው አንዲት መነኩሲት ናት፡፡ እዚህ ሁሉም ናቸው… (ገጽ 94-98 - አጽንዖት የግል)፡፡

ከዚህ በላይ የሰፈሩት ሐሳቦች የተወሰዱት ከአምስት ተከታታይ ገጾች ቢሆንም ቀደም ሲል እንደተባለው ሙሉ ሐሳቡን ማስፈር አስፈላጊ ሆኖ አልተገኘም፡፡ አንባቢ በራሱ እነዚህን ገጾች ቢመለከት ግን በዚህ ጽሑፍ ላይ ከሰፈሩት የተሻለ ነገረ እንደሚያገኝ ይታመናል፡፡

ቀደም ሲል እንዳደረገው «በአንዳንድ ገድሎች አባ ዮሐነስ የመጡት ደብረ አስቦ ከተመሠረተ በኋላ ነው፡፡ እዚህ ግን ገና ሳይመሰረት ነው» (ገጽ 114 - አጽንዖት የግል) የሚለውን ያሰፈረውን የዳንኤልን ሐሳብ የተከተለ ልባም አንባቢ ገድሎች ደስ ያላቸው የሚያሰፈሩ ደስ ያላላቸውን የሚያሰቀሩ መሆናቸውን ለመረዳት ጊዜ አይወስድበትም፡፡

3

ከዚህ ወጣ በማለት ደግሞ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሕጻን ሳሉ ተከሰቶ ስለነበረው ረሃብ አደረጉት ተብሎ ወደሚታመነው ተአምርና፤ ዲቁና የተቀበሉበትን ዘመን በተመለከተ ወደ ሰፈረው ስንሄድ፤ «… የአንድ ዓመት ሕጻን እያሉ የተከሰተውን ረሃብ የዳጋው በ11 ዓመት ከ11 ወራቸው ሲያደርገው የፓሪሱ (2ኛ) በ11 ዓመት ከ3 ወር ያርገዋል፡፡ ዲቁና የተቀበሉበትን እድሜ የዳጋው በ14 ዓመት ሲያደርገው የፓሪሱ (2ኛ) ቅጅ ግን በ14 ዓመት ያደርገዋል» በሚል የሰፈረው እናገኛለን (ገጽ 99-100 - አጽንዖት የግል)፡፡

በዚህ ሰፍራ ላይ ደግሞ ሁለት ታሪኮችን መሠረት አደርጎ የቀረበውን የገድሎቹን ልዩነት እናያለን፡፡ የመጀመሪያ በሕጻንነታቸው ተከስቶ ስለነበረው ረሃብ የሚመለከተው ሲሆን እሱም በሦስት የእድሜ ለዩነት ነው የቀረበው፡-

1. እንደ ዳንኤል ሐሳብ ከሆነ ረሃቡ የተከሰተው የአንድ ዓመት ሕጻን ሳሉ ነው፣
2. የዳጋው ቅጅ ደግሞ በ11 ዓመት ከ11 ወራቸው ያደርገዋል፣
3. የፓሪሱ (2ኛ) ቅጅ በበኩሉ ወደ 4 ዓመት ከፍ ያደርገዋል፡፡

ሌላው ደግሞ ዲቁና የተቀበሉበትን እድሜ በተመለከተ ያለው የሐሳብ ልዩነት ነው። እሱንም በ14 እና በ4 ዓመት የተቀመጠ መሆኑን ማየት ይቻላል። ይህም ገድሎቹ ላይ የተሠራውን ለውጥ የሚጠቁም ነው።

4

ከዚህ ሌላ ደግሞ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ሚስት ያረፈችበትን ጊዜ በተመለከተ የሰፈረውና «የደብረ ሊባኖሱ ቅጅ ሚስት እንደታጨላቸው ነገረ ግን ከወላጆቻቸው በፊት ማረፏን ይተርካል። ሌሎቹ ቅጅዎችም ከወላጆቻቸው ቀጥላ ወዲያው መሞቷን ብቻ ይተርካሉ» የሚለውም በገድሉ ላይ የተሠራውን ለውጥ ያሳየናል (ገጽ 103 - አጽንዖት የግል)።

አንድ ታሪክን መሠረት አድርገው የተለያየ ነገር እያስነበቡ ያሉት የገድለ ተክለ ሃይማኖት ልዩ ልዩ ቅጂዎች የተሠሩ ለውጦችን በዚህ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም መንገዶች ያሳያሉ። ከእነዚህም ውስጥ በዋልድባው ገድል ላይ ለሞተሌሚ የነገረችው አንዲት ሴት ስትሆን (ገጽ 94)፤ በሐይቅ ቅጅ ላይ ደግሞ ለሞተለሚ እንደነገሩት የሚገልጸው መኳንንት ናቸው (ገጽ 106)።

5

«የመጀሪያውና በ1417 ዓመተ ምሕረት በደበረ ሊባኖስ የተጻፈው ገድለ ተክለ ሃይማኖት የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የሰሜን ጉዞ መጨረሻ ሐይቅ ነው ይላል» የሚለው ዳንኤል ክብረት «የሐይቁ ግን ታሪኩን ወደ ደብረ ዳሞ ወስዶታል» በማለት የተሠራውን ለውጥ አስቀምጧል (ገጽ 107)። በግርጌ ማስታወሻ ካሰፈራቸው ሐሳቦች መካከልም፤

> ከዚህ ዘመን ጋር ተቀራራቢ በሆነ መልኩ በዚህ ስም የሚጠራ [የ]እስክንድርያ ሊቀ ጳጳስ አልነበረም። ሚካኤል 5ኛ የተባሉት 71ኛ የእስክንድርያ ፓትርያርክ ከ1092-1102 የነበሩ ሲሆኑ ሚካኤል ስድስተኛ ደግሞ ከ1145-1146 የነበሩ ናቸው። ሚካኤል ስድስተኛም ከ300 ዓመታት በኋላ ከ1476-1478 የነበሩ ናቸው (Coptic Encyclopedia, vol. 5, 1614-1616) ከእነዚህ ከሦስቱ ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ዘመን ጋር የተቀራረቡ የሉም፤ ገድሉን የጻፈው ሰው ስም ሳያሳስት አልቀረም፤

በማለት የተሠራውን ለውጥ አሳየቷል (ገጽ 112 የግርጌ ማስታወሻ ቍጥር 256)።

6

ዳንኤል በልዩ ልዩ ቦታዎች ሊያሳይ የሞከረው አንዱ ነገር የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የጋብቻ ሁኔታን በተመለከተ ነው።[16] እሱንም በተመለከተ የተሠራውን ለውጥ የመንዙ ገድለ ተክለ ሃይማኖት «... ጋብቻው መፈጸሙን አይነግረንም...» በማለት ይጀምርና «ይህ የጋብቻ ክርክር በደብረ ሊባኖሱ ቅጅ ላይ የለም። የደብረ ሊባኖሱ ቅጅ በአጭሩ የመታጨቷን ነገር ይነግረንና ከጥቂት ጊዜ በኋላ ማረፏን ይተርካል። የሚጣቀና የሐይቁ

[16] በአቡኑ የጋብቻ ሁኔታ ላይ ትኩረት ያደረገው ወዶ ሳይሆን መልስ ልሰጣቸው ብሎ የተነሣቸው ሰዎች ቀድመው ያነሡት በመሆኑና እሱን በተመለከተ የሆነ ነገር ማለት ግድ ስለሆነበት ነው።

ግን ጋብቻውን በዝርዝር ያቀርቡታል» የሚለውን በማስከተል የተሠራውን ለውጥ አስቀምጠታል (ገጽ 124)።

7

ገድሎቹ ውስጣቸው ባሰፈሩት ታሪክ ብቻም ሳይሆን ተጻፍንበት በሚሉት የዘመን ገለጻቸው ላይም ሊታመኑ የማይገባቸው መሆኑን ዳንኤል እንዲህ ያስነበባል፤ «መጽሐፉ የተገለጠው (የተጻፈው) በ290 ዓመት ከ9 ወር ላይ በሰባተኛው ትውልድ መሆኑን ይነግረናል። ዘመኑ የተቈጠረው ቅዱሱ ካረፉበት ይመስላል። እንደዚያ ከሆነ ወደ 1595 ዓመተ ምሕረት አካባቢ ይሆናል። ይሄ ደግሞ በሌሎች ምንጮች ከምናገኘው 1507 ዓመተ ምሕረት ጋር ይጋጫል» (ገጽ 127)።

ገድሉን በዚህ ሐሳቡ እንዳናምነው የሚያደረገን ነገረ የምናገኘው ታሪክ አሳሰቶ ወይም ጨምሮ አይደለም። ጸሐፊው ራሱ እየጻፈው ሳለ የጻፈበትን ዘመን የሚያሳስት አድርጎ በማስቀመጡ እንጂ። ይህን በማድረጉ የሚያገኘው ትርፍ ግልጽ ባይሆንም በዚህ በትንሹ ነገር ያልታመነ በትልቁ ነገሮች እንዴት ሊታመን ይችላል?

8

በሌላም መልኩ ደግሞ ይሄማ የእከሌ ስሕተት ነው በሚል የሚጠቁመው ነገር አለ፤ «ቅጂው የ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው። የሚከተለውም የደብረ ሊባኖሱን መንገድ ነው። ፍሬምናጦስ የመጣበትን ዘመን በ257 ዓመት ያደርገዋል። የአባ ጌርሎስንም ስም አንዳንድ ጊዜ ጎርጎርዮስ ይለዋል። ይህም በዘመናት ውስጥ ገልባጮች የሚሠሩትን ግድፈት ያሳየናል» (ገጽ 139-140)። «... ግንቦት 12 ማለት ሲገባው ግንቦት 16 የሚለው የገልባጭ ስሕተት ነው...» (ገጽ 171)። እዚህ ጋር የሚነሣው ጥያቄ በገልባጭም ይሁን በጸሐፊው ስሕተት ገድሉ በውስጡ ስሕተት ከያዘ «ቅዱስ» መጽሐፍ ሊባል ይችላል ወይ? የሚለው ነው።

9

ከዚህ ወጣ በማለት አንድ ታሪክን መሠረት አደርገው የጻፉ ሦስት ገድሎች መካከል ያለውን ያለመግባባት ነገር ስንመለከት ነገሩ እንዴት ነው? የሚል ሐሳብ ወስጥ መግባታችን አይቀርም። ለዚህም ዳንኤል የአቡነ ተክለ ሃይማኖት እናት ሞተለሜ ሚስቱ ሊያደረጋት ሲል የጸለየችውን ጸሎት ያሰፈረውን መመልከቱ ጠቃሚ ነው፤

1. በዮሐንስ ከማ ቅጅ፤

ቅዱስ ሚካኤል ሆይ ‹እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ልጅ ስጠኝ፤ ካልሆነ ግን ማኅጸኔን ዝጋው› ስል ቃል ኪዳንን ከአንተ ጋር የገባሁ አይደለሁምን?[17] እኔስ

[17] በዚህ ጸሎት መሠረት ልጅ መስጠት አልያም ማኅጸንን መዝጋት የእግዚአብሔር ሳይሆን የሚካኤል ሥራ ሆኖ ይታያል። እንዲህ ያለውና ለፈጣሪ የሚገባውን ለፍጡር የመስጠት ነገር በገድለ ተክለ ሃይማኖት ውስጥ ብቻ ሳይሆን በብዙ ገድላትና ድርሳናት ውስጥ ይታያል። እነዚህ ነገሮች በ«አዋልድ» መጻሕፍት ውስጥ በብዛት መታየት እግዚአብሔር ለፍጡራኑ የሥራ ክፍፍል አድርጎ የተቀመጠ ይመስላል። አንዳንድ ጊዜም አንዱ ሥራ (ለምሳሌ ልጅ ለሌላቸው ልጅ መስጠት) የልዩ

ከባሌ ጋር ካልሆነ በቀር ሌላን መኝታ አላወቅም። ከድንግልናዬ ጀምሮም የእግዚአብሔር ሰው ከሆነው ከወዳጄ ከዘርዐ ዮሐንስ ጋር ካልሆነ በቀር መኝታዬን አላረከስኩም (ገጽ 361)።

2. በጣና ቂርቆሱ ቅጅ፤

ሌሊቱን ሁሉ ስትጸልይ አደረች። እንዲህ እያለችም ወደ እግዚአብሔር ጸለየች፤ ‹አቤቱ ስንፍናንዬንና በደሌን ለምን አሰብከ? ወዳጄንና ባለቤቴንስ ለምን አላሰብከውም? ከእርሱ በቀር ከሌላ ወንድ ጋር መተኛትን አላወቅምና። አቤቱ ከዚህ አረማዊ እጅ አድነኝ፤ አስጥለኝም። በእውነት አቤቱ አንተ ረዳቴ ነህ፤ ስደተኛ ባሪያህን አድናት።›› ሣራን ከፈርዖን እጅ እንዳዳንካት፤ አስቀድሜ በንጹህ ጋብቻ ተወሰንኩ፤ እነሆ አሁን ደግሞ ከርስቶስን ለካደ ሰው በርኩሳን አማልክት ሕግ ሚስት እሆነ ዘንድ አመጡኝ። ሕግህን ከካደ ሰው ጋር አንድ ከምሆን እኔስ ነፍሴን በዚህች ሌሊት ብትወስዳት እሻለሁ (ገጽ 361)።

3. በደብረ ሊባኖሱ ሁለተኛ (የእጨጌ ጴጥሮስ) ቅጅ፤

የፍጥረት ሁሉ አምላክ የሆንክ አቤቱ፤ ሁሉን ትችላለህ፤ የሚሣንህ ነገር የለም። ያለህበትና የሌለህበት ተብሎ የሚለይ የለም። መለኮትህ በአገሮች ሁሉ የሞላ ነው። ሣራን ከጌራራው ንጉሥ ከፈርዖን እጅ ያዳንካት አንተ ነህ። ዳንኤልንም ከተራቡ አንበሶች አፍ ያዳንከው አንተ ነህ። ሶስናን ከክፉዎች መምህራን እጅ ያዳንካት አንተ ነህ። ሦስቱን ሕጻናት ከባቢሎን እሳት ያዳካቸው አንተ ነህ። ጥንትም አንተ ነህ፤ ዛሬም አንተው ነህ። የማዳንህም ኃይል በእኔ ላይ ይገለጥ። አቤቱ ለስምህ ክብርን ስጥ። ስደተኛ ባሪያህንም በተኩላዎች እጅ አትተዋት። አንተስ ሚካኤል ሆይ ዝም ማለትህ ለምንድን ነው?[18] ጸጥ ማለትህስ ለምንድን ነው? በአገልጋይ ላይ ይህ ሁሉ መከራ ሲመጣባት። ካንተ ጋር የገባሁት ቃል ኪዳን ረሳኸውን? ተዝካርህንስ በማድረጌ የተነሣ ይህ ሁሉ መከራ ይድረስብኝ? ልታከብረኝስ ሲገባ መከራ ውስጥ ትጥለኝ? ደስ ልታሰኝኝስ ሲገባ ታሳዝነኛለህን? እንዲህስ አይሁን ሚካኤል ሆይ፤ ችግረኞችን የምትረዳ ነህና እርዳኝ፤ ሊወድቁ የደረሱትን የምትደግፍ ነህና ደግፈኝ፤ ይህንም ስትጸልይ ሚካኤል ተገልጦ[19] ታየት (ገጽ 362)።

ልዩ ቅዱሳን ግብር ሆኖ ሲገለጽ ሁሉም በአንድ ሥራ ላይ ተሾመው ይሆን? ያስብላል። ይህ ሁሉ ግን ዳንኤል ከብረት እንዳለው «... ፉክክሩ ያመጣው ...» ጣጣ ነው (ገጽ 567)።

[18] እግዚአብሔርን ‹ጥንትም አንተ ነህ ዛሬም ያው አንተ ነህ... ማዳንህ በባሪያህ ይገለጥ› ብላ ስታበቃ መልሳ ደግሞ ‹አንተስ ምነው ዝም አልክ?› በሚል ሚካኤልን መጥራት ያስፈለጋት አንዱ ባይሰማኝ በሌላ ልሞክር ብላ ይሆን? ወይስ ቅድስት እንደሆነችና የመጽሐፍ ቅዱስ እውቀት እንዳላት የሚነገርላት ይህቺ ሴት «ሥጋ ሁሉ ጸሎትን ወደምትሰማ ወደ አንተ ይመጣል» (መዝሙረ ዳዊት 64÷2) የሚለውን ቃለ እግዚአብሔርን ስለማታውቀው ነው?

[19] የ«አዋልድ» መጻሕፍት ባሕርይ እዚህ ጋር ይታያል። «አዋልድ» መጻሕፍት ማስተላለፍ የሚፈልጉት ለሰው ልጆች ቅርብ የሆኑት ፍጡራኑ በመሆናቸው የምንፈልገውን ነገር ሁሉ እነርሱን እንጠይቅ የሚለውን ነው። በዚህም የጸሎት ስፍራ ወደ እግዚአብሔር እና ወደ ሚካኤል የጸለየች ሲሆን ጸሎት ሰሚና ፈጥኖ መላሽ ሆኖ እንዲቀርብ የተፈለገው እግዚአብሔር ሳይሆን

የጸለየቸው ሴት አንድ፣ የጸለየችበትም ምክንያት አንድ ሆኖ ሳለ በሦስት መዛግብት የሰፈረው ጸሎት ግን እንዲህ ባለ ሁኔታ የማይገናኝ ሆኖ መገኘቱ ምክንያቱ ምንድን ነው? ቢባል የሚኖረው መልስ ገድሎቹን የወደደ ሰው ደስ እንዳለው ስለሚለዋውጣቸው ነው የሚል ይሆናል።

አሁንም በተመሳሳይ ሁኔታ ታሪኩ አንድ ሆኖ ሦስት ገድሎች እንዴት ባለ ሁኔታ እንደዘገቡት ዳንኤል ያሰፈረውን እነሆ። ታሪኩ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት እናት እግዚእ ኀረያ ጸሎቷን ካቀረበች በኋላ ወደ ባለቤቷ ትመለሳለች። ወደ ባለቤቷ ከተመለሰች በኋላ ያጋጠማትን ነገር ነው በሦስቱ ገድሎች የምናየው፤

1. በእጨጌ ዮሐንስ ከማ ቅጅ፤

እርሷም ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብታ ሰላደረገላት ሁሉ እግዚአበሔርን እያመሰገነች ቆመች። ባሏም እያጠነ ዑደት ያደርግ ዘንድ ወጣ። አንዲት የተጌጠች ሴት ቆማ ስትጸልይ አያት። እርሱም ‹ይህቺ ሴት ማን ናት? እንዴትስ አሽከሮችና ደንገጡሮች የሏትም?› ብሎ እያደነቀ ዕጣኑን አሳርጎ ወደ ውጭ ወጣና ተቀመጠ። እርሷም መጥታ ከንብንቧን ገልጣ ተባረከች። እርሱም ‹አንቺ ከወዴት ነሽ?› አላት። እርሷም ሞተለሚ አገኘኝ፤ ሴትና ወንድ አሽከሮቼን፣ ሀብቴንም ሁሉ ወሰደብኝ። እኔንም እግዚአብሔር አዳነኝ። እነሆም ጸጋ ዘአብ የተባለ ሰው ሚስቱ እንደተማረከችበት ሰማሁ፤ እኔም ሚስቱ እሆን ዘንድ መጣሁ› አለችው። እርሱም ‹ክፉ ሐሳብን እንደዚህ አድርገሽ አሰብሽ። እርሱን ግን ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ገብቶ ሌላ ሚስት አላገባም፣ ክህነቴንም አላፈርስም ሲል ሰማሁት› አላት። እርሷም ‹ከምርኮ ይመልስለታለን?› አለችው። እርሱም ‹ከሞተችም በኋላ እንኳን ቢሆን ለእግዚአብሔር የሚሣነው ነገር የለም› አላት። ደግሞም ‹ቃልሽ እንደ ቃሏ ይመስላል› አላት። እርሷም በልቧ ፈገግ አለች። የሃይማኖቱንም ጽንአት ተረዳች። የፊቷን መሸፈኛ ገለጠችው። ‹እኔ ሚስትህ እግዚእ ኀረያ ነኝ፤ እግዚአብሔር በእርሱ የሚመካውን አይጥለውምና› አለችው (ገጽ 368)።

2. በዋልድባው ቅጅ፤

(ጸጋ ዘአብ) በዚያ ቀን በቤተ ክርስቲያን አያጠነ እንዳለ ሚስቱ እንደተመለሰች ነገሩት። ከዚያ በኋላ (አገልግሎቱን) ፈጽሞ ወደ ቤቱ መጣ። ባያትም ጊዜ ደስ ተሰኝቶ አምላኩን አመሰገነ። መልአኩ ነጠቆ እንዳመጣት፣ ስለምትወልደው ልጅም እንደነገራት ተረከችለት። ደስ ተሰኝተውም መልሶ ስላገናኛቸው እግዚአብሔርን አመሰገኑት (ገጽ 368)።

3. በጣና ቂርቆሱ ቅጅ፤

በዚህም ጊዜ ባሏ ማዕጠንት እያጠነ ወጣ። እንደ ነገሥታት ልጆችም በአልባሰ ወርቅ ተጊጣ አያት። ደንግጦም ይህቺ የተከበረች ሴት ከየት ናት? ደግሞም የሴትና የወንድ አሽከሮች የሏትም፤ ተልዕኮውን ፈጽሞ ሊያደንቅ ወጣ። ፊቷንም ተሸፋፍና ከእርሱ ዘንድ ቡራኬ ተቀበለች። እርሱም በዚህ ታላቅ ክብር

ሚካኤል በመሆኑ ወደ እግዚአብሔር በጸለየችበት ቦታ መልስ ስታጣ ወደ ሚካኤል ስትጸለይ ግን «... ሚካኤል ተገልጦ ታየት ...» በሚለው ማሳየት የተፈለገው ያንኑ ነው።

> የምትታዩ አንቺ ከወዴት ነሽ? ምነውስ ደግሞ የወንድና የሴት አሽከሮች የሉሽምሳ? አላት፡፡ ያን ጊዜም ፊቷን ገለጠችና ታየቸው፡፡ ‹ወንድሜ ሆይ እኔኮ ሚስትህ ነኝ፤ እግዚአብሔር ከዚህ ዐላዊ እጅ አስጣለኝ፤ ካንተ ከተለየሁ በኋላ ከመልካም በቀር አንዳችም ክፉ ነገር አላጋጠመኝም› አለቸው፡፡ እግዚአብሔር ያደረገላትን ነገር ሁሉ ነገረቸው፡፡ የእግዚአብሔርንም ታላቅነት እርስ በእርሳቸው ተነጋገሩ (ገጽ 371)፡፡

በእነዚህ ሦስት ቅጅዎች ውስጥ የሚነበበው ታሪክ አንድ እሱም እግዚእ ኀረያ ከጸጋ ዘአብ ጋር ዳግመኛ መገናኘታቸውን ቢሆንም በውስጡ ያሉት ነገሮች ግን ምን ያህል የተለያዩ እንደሆኑ ማየት ገደላት በየጊዜው የሚሠራባቸው ለውጥ መኖሩን በሚገባ ያሳያል ተብሎ ተስፋ ይደረጋል፡፡

❶❼

በመጨረሻም ገድሎች ብቻ ሳይሆኑ በቤተ ክርስቲያን በብዙ የሚታመነው ለብዙ ነገር ተጠቃሽ የሆነው ስንክሳርንም ችግር እንዲህ አሳይቶናል፤

> ስንክሳር ረፍቱን ሐምሌ 26 ያደርገዋል፡፡ በዚህ ድርሳን ላይ ግን ታኅሣሥ 18 ነው፡፡ በርግጥ ስንክሳር በታኅሣሥ 18 ቀን የአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን መታሰቢያ ነው ይላል፡፡ ነገር ግን ዕረፍቱንና ታሪኩን በሐምሌ 26 ነው የሚሠራው፡፡ ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ የደረሰው አርኬ (የዐሥራ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ቅጅ) እና አንድ በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተጻፈ አርኬ በታኅሣሥ 18 ነው ለአባ ሰላማ አርኬ የሚሠራው፡፡... ከእርሱ ዘመን በፊት በነበሩት ድርሳናት ላይ ተመሥርቶ አርኬውን ያዘጋጀው ዐፄ ዘርዐ ያዕቆብ አባ ሰላማና ፍሬምናጦስ አንድ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ ገድለ አባ ሰላማም ዕረፍቱን በሐምሌ 26 ቀን ያደርገዋል፡፡ አንዳንድ የታሪክ ባለሞያዎች ፍሬምናጦስና አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ሁለት የተለያዩ ጳጳሳት ናቸው ይላሉ፡፡ ለዚህ የሚያቀርቡት አንዱ ማስረጃ የዕረፍታቸው ቀን መለያየት ነው፡፡ እንደ እነርሱ አባባል ፍሬምናጦስ ታኅሣሥ 18 ሲያርፈ አባ ሰላማ ግን ሐምሌ 26 ዐርፏል፡፡ በሌላም በኩል ይህ ጥንታዊ ድርሳን ‹ሰላማ› ወይም ‹ከሣቴ ብርሃን› የሚለውን ስም አያነሣውም፡፡ ምናልባት ግን ከፍሬምናጦስ በኋላ ሰላማ የሚባል አባት በኢትዮጵያ ሳይሾም አይቀርም፡፡ ሐምሌ 26 ቀን የእርሱ ዕረፍት መሆን አለበት፡፡ ስንክሳሩን ያዘጋጀው ሰው የአባ ሰላማን ታሪኩን ሲያጣው የፍሬምናጦስን ታሪክ ወስዶ ጽፎለት ይሆናል (ገጽ 333-334 ግርጌ ማስታወሻ ቍጥር 917)፡፡

<u>የጎደሉ</u>

ቀደም ባሉት ሁለት እርዕስት ውስጥ ገድሎች ጭማሪ ሲያስፈልግ የሚጨመርባቸው፣ ደግሞም መለወጥ አለበት ተብሎ የሚታመን ነገረ ከተገኘ የሚለወጥባቸው መሆናቸው ቀርቦ ነበረ፡፡ በዚህ ርዕስ ስር ደግሞ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ከታሪኩ ማጉደል ሁሉ የሚከሰት መሆኑን ዳንኤል ገድለ ተክለ ሃይማኖት ላይ የተሠራውን ሥራ ይፋ ያደረገውን መነሻ በማድረግ አብረን እንመለከታለን፡፡

❶

የገድሎች ጸሓፍት በብዙ የሚጨነቁት ለቃለ እግዚአብሔር ታማኝ ለመሆን ሳይሆን ገድሉ ለሚጻፍለት አካል «ቅድስና» ነው፡፡ በእነርሱ እምነት የገድሉን ባለቤት ቅድስና የሚያጎድል መስሎ የሚታያቸው ነገር ካለ ከድሉ የሚጎድል ሲሆን የ«ቅዱሱን» ቀድስና ከፍ ከፍ ያደርጋል ተብሎ የሚታመን ነገር ከተማቸው ደገሞ እውነት ባይሆንም እንኳ[20] የገድሉ አካል ከመሆን የሚያግደው ነገር የለም፡፡

እንዲህ ያለ ነገር ዳንኤል ያሰፈረውን ከዚህ በታች አቅርበነዋል፤ ሐሳቡ በልዩ ልዩ ገጾች የሰፈረ በመሆኑ ሁሉን እንዳለ ማቅረቡ ወረቀት መፍጀት ነው በሚል ጥቂት ነጥቦች ላይ ትኩረት ለማድረግ ተሞክሯል፤

- «... በሌላ በኩል ደግሞ የዘማዊቷን ሴት ፈተና <u>አልመዘገበውም</u>» (ገጽ 87)፡፡
- «... በዞረሬ የፈተነቻቸው ሴት ታሪክ <u>የለም</u>...» (ገጽ 88)፡፡
- «በጉባ ላፍቶው፣ በሚጣቁና በወይንዬ ተክለ ሃይማኖቱ ቅጅዎች ላይ <u>ተደመስሷል</u>፡፡ በሁለተኛው የደብረ ሊባኖሱ ቅጅ ላይ ታሪኩ <u>አልተካተተም</u>...» (ገጽ 407)፡፡
- «... የፓሪሱ (2ኛ) ቅጅም አንዳንድ ቦታ ላይ <u>ተደምስሷል</u>፡፡ የደጋውም በአንዳንድ ቦታዎች <u>ድምሰሳ ገጥሞታል</u>፡፡ በሚጣቁ ቅጅም የተወሰነው የታሪኩ ክፍል <u>እንዲጠፋ ተደርጓል</u>፡፡ በጉባ ላፍቶው ቅጅ ላይም <u>ይሄው ይታያል</u> ...» (ገጽ 408-409)፡፡
- «... ይህንን ትረካ ግን የኋላ ሰዎች <u>ደምስሰውታል</u>...» (ገጽ 111)፡፡
- «የእጨጌ ዮሐንስ ከማው፣ የመንዙና የወይንዬው አንዳንዱን ክፍል <u>ደምስሶታል</u>፡፡ የጉባ ላፍቶው አልፎ አልፎ <u>ድምሳሴ ገጥሞታል</u>...» (ገጽ 415 ግርጌ ማስታወሻ ቍጥር 1242)፡፡
- «የሚጣቅ ተክለ ሃይማኖቱን የኋላ ሰዎች <u>ለመሠረዝ ሞክረዋል</u>፡፡ ይህ ሥረዛ በእጨጌ ዮሐንስ ከማ፣ በደጋው፣ በሚጣቅ ተክለ ሃይማኖቱና በወይንጌ ተክለ ሃይማኖት ቅጅዎች ላይ የመሠረዝ ዕጣ ገጥሞታል፡፡ ሥረዛው የቅርብ ዘመን አይደለም፡፡ ምክንያቱም በ1903 ዓመተ ምሕረት ከኢትዮጵያ የወጣው የፓሪሱ ቅጅም ይሄው ሥረዛ ገጥሞታልና፡፡... በተመሳሳይ ዘመን በሸዋና በጣና አካባቢ ያሉ ቅጅዎችን እንዲሠርዙ ያደረገ አካል ያለ ይመስላል» (ገጽ 103)፡፡

ከእነዚህ ነጥቦች «አልመዘገበውም»፣ «የለም»፣ «ተደመስሷል»፣ «አልተካተተም»፣ «ድምሰሳ ገጥሞታል»፣ «ደምስሶታል»፣ «ለመሠረዝ ሞክረዋል»፣ «እንዲጠፋ ተደርጓል» የሚሉት ቃላት እናገኛለን፡፡ ከእነዚህም ድምሳሴውም ሆነ አለማካተቱ እንዲሁም መተዉ

[20] ቀደም ሲል አቡነ ተክለ ሃይማኖት በዓመት ሦስት ጊዜ ኢየሩሳሌም ደርሰው ይመጡ ነበር የሚለው በገድላት ውስጥ መጻፉን ተመልክተን ነበር፡፡ ነገር ግን ራሱ ዳንኤል አንዳንድ ሊቃውንት ያላቸውን ተተግኖ እንዳሰፈረው «ቅዱሱ ከኢትዮጵያ አልወጡም» ሲል በገጽ 587 ላይ ደግሞ «አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወደ ኢየሩሳሌም መጓዛቸውን ለመቀበል እንቸገራለን» በማለት ሐሳቡን አስፍሯል፡፡ ስለዚህ ገድላቱ የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን ቅድስና ከፍ ለማድረግ በዓመት ሦስት ጊዜ ያህል ኢየሩሳሌም አድርሰው ሲያመጧቸው እውነታው ግን አቡኑ አንድም ጊዜ ከኢትዮጵያ ወጥተው የማያውቁ መሆኑ ነው፡፡

የተከሰተው በአጋጣሚ ሳይሆን ሆነ ተብሎ መሆኑን መረዳት እንችላለን፡፡ ለዚህም የሚቀርብ ምክንያት መኖሩን ዳንኤል፤

- ‹‹ምናልባት የኋላ ዘመን ጸሓፍት ነውር መስሏቸው አውጥተዉት ይሆናል›› (ገጽ 407 - አጽንዖት የግል)፣
- ‹‹የኋላ ገልባጮች ቅዱሱን የተዳፈሩ መስሏቸው ሳያስቀሩት አይቀርም›› (ገጽ 105 - አጽንዖት የግል)፣
- ‹‹ምናልባት ቅዱሱ በዞረሬ ከነበረችው ዘማዊት ሴት የገጠማቸውን ፈተና መጻፍ እንደ ማዋረድ የተመለከተ ሰው ብራናውን ለመፋቅ ሞክሯል›› (ገጽ 110 - አጽንዖት የግል)፣

በማለት አቅርቦታል፡፡

‹‹ነውር›› በሚል የተገለጸው ‹‹የቅዱሱን›› ቅድስና ጥያቄ ምልክት የሚከት መስሎ ስለታያቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ቀደም ባለው ዘመን የነበሩ ሰዎች (አሁንም እርሾው አለ) ‹‹ቅዱሳን›› የቅድስና ልኬት የሚታየው ምንም ዓይነት ፈተና ቢመጣባቸው ፈታቸው ሳይፈታ ሁሉን በድል የሚወጡ እንደሆኑ ናቸው በሚለው ነው፡፡

በዚህ ታሪክ ውስጥ የቀረበችው ዘማዊት ሴት ግን አቡነ ተክለ ሃይማኖትን መፈታተን ብቻ ሳይሆን እንዲያምነቱ ያደረገች በመሆኑ ‹‹ቅዱሱ›› ይህን ያህል ተፈትኖ ማየት ለ‹‹ቅዱሳን›› አድናቂዎች ራሱ ፈተና በመሆኑ ከየብራናው ላይ በመፋቀና ታሪኩን ባለማካተት ሐሳቡን በተዘዋዋሪ መንገድ መቃወማቸውን አሳይተዋል፡፡ ይህም አቡነ ተክለ ሃይማኖት እንደ አዳም ልጅ ሥጋ ለባሽ ሳይሆኑ ምንም ዓይነት ፈተና ቢመጣ የማያንገራግሯቸው የፍጽምና ደረጃ ላይ የደረሱ አደርገው የሳሏቸው በመሆኑ የተፈጠረ ችግር ነው፡፡

2

ከዚህ ብዙም የማይርቀውና የአቡነ ተክለ ሃይማኖት የጋብቻን ሁኔታ በተመለከተ የሰፈረውን ከዚህ በታች ለማስቀመጥ ተሞክሯል፤

ምንም እንኳ በቤተሰቦቻቸው ጫና ቢሆንም አቡነ ተክለ ሃይማኖት ትዳር ይዘው ነበር፡፡ ዳንኤል ክብረት እንደ ጻፈው ከሆነ ግን ‹‹ከሚጣቅ ተክለ ሃይማኖቱ፣ ከወይንየውና ከመንዙ ቅጅዎች እንዲሁም በእነርሱ መንገድ ከተጻፉት በቀር የሚተርክ የለም፡፡ በሌሎች ቅጂዎች ሚስት እንዳጨለት ብቻ ይነግረናል፡፡ የጋብቻውን ሕይወት በተመለከተ እንዲህ በዝርዝር የሚገለጽ ግን የለም፡፡ የደብረ ሊባኖሱ ቅጅ ሚስት እንደታጨላቸው ነገር ግን ከወላጆቻቸው በፊት ማረፏን ይተርካል፡፡ ሌሎቹ ቅጅዎችም ከወላጆቻቸው ቀጥላ ወዲያው መሞቷን ብቻ ይተርካሉ›› (ገጽ 103)፡፡

ቀደም ሲል እንደተባለው አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቤተሰቦቻቸው ግድ ብለዋቸውም ቢሆን በመሠረቱት ጋብቻ ለጥቂት ጊዜ አብረው መኖር ጀምረው ነበር፡፡ በዚህ ወቅትም ‹‹ለሦስት ቀን››ም ቢሆን ወሲባዊ ግንኙነት ፈጽመው ነበር፡፡ በዳንኤል ዘገባ መሠረት ‹‹ይሄ ታሪክ በሚጣቁ ቅጅ ላይ ቢገኝም ነገር ግን የኋላ ሰዎች በከፊል ደምስሰውታል፡፡ ታሪኩን ማሟላት የሚቻለው ከጉባ ላፍቶው ቅጅ... [ነው]፡፡ እርሱም ቢሆን አልፎ አልፎ የመደመሰስ ዕጣ ገጥሞታል››፡፡ ለዚህም ቢሆን የሚቀርበው ምክንያት ቀደም ሲል ከቀረበው ምክንያት የተለየ አይደለም፤ ‹‹በኋላ ዘመን የተነሡ ሰዎች ይሄን ታሪክ ለአቡነ ተክለ ሃይማኖት መንገር ነውር ሳይመሰላቸው አልቀረም›› (ገጽ 397)፡፡ ስለዚህ


ምንም እንኳ ታሪኩ እውነት ቢሆንም የማጥፋት ርምጃ በመውሰድ ለ«ቅዱሱ» የቅድሰናን ደረጃ ከፍ ማድረግ[21] የሚችሉበትን መንገድ ቀየሱ፤ አደረጉትም!

ዳንኤል ድምሳሴ አጋጥሚቾዋል በሚል በፎቶ ይፋ ካደረጋቹው ገድሎች መካከል ከዚህ በታች ያሉት ይገኙበታል፤




በሚጣቁ ተክለ ሃይማኖት ገድል ብራና ላይ የተደረገው ድምሳሴ(ቅጠል


[21] በቤተ ክርስቲያናችን እንደ ጎጢአት ከሚታዩ ነገሮች ውስጥ አንዱ ጋብቻ ይመሰላል፡፡ ሰዎች በጋብቻ ሕይወት ተሳስረው ለመኖር አስከሚፈሩ ደረስ እንዲህ ያሉት ታሪኮች ያለማግባት የቅድስና ማግባት ደግሞ ቅድስናን የማጣት ሕይወት እንደ ሆነ አስመሰለው እየሰበኩ ይገኛሉ፡፡



በጓጋው ቅጅ ላይ የተደረገው ሥረዛ(ቅጠል 34ለ)



የፓሪሱ(2ኛ) ቅጅ፣ 48ሀ ያጋጠመው ድምሰሳ



ከአጨጌ ዮሐንስ ከማ ቅጅ የተደመሰሰው ገጽ(ቅጠል 17ሀ)

ቀደም ሲል በቀረቡት ሦስቱ ነጥቦች (የተጨመሩ፣ የተለወጡና የጎደሉ በሚሉት) ውስጥ እንደተመለከትነው ገድላት የአንድ አካል ማስታወሻ ደብተር ይመስል የወደደ እየተነሣ የሚጨመርባቸው፣ ደስ ያለው የሚለውጣቸው፣ ታሪካቸውን የጠላው ደግሞ የሚያጎድላቸው ናቸው።

በዚህ መሠረት ከሄድን ገድሎች አይደለም ለመንፈሳዊው ነገር ለታሪክና ለሌሎች ጥናቶችም ቢሆንም ልብን የሚያሳርፍ ነገር እንዳናገኝባቸው «የኋላ ሰዎች» በሚል ሰበብ የሚቀርብባቸው አካላት አድርገውናል ማለት ነው። በመሆኑም አንድን ገድል መነሻ በማድረግ አስተማማኝ ስለሆነው የጽድቅ መንገድ፣ የቅድስና ጎዳና ከዚህም በላይ እግዚአብሔር የሚገኝበትን ሁኔታ ለማወቅ ከባድ ነው ማለት ነው። ስለዚህ እንዴት ነው በገድሎች ለማመን የምንበረታታው?

ጉርሻ፤ ተጠመቀ ስለሚባለው «ሰይጣን»

ገድለ ተክለ ሃይማኖትን መነሻ በማድረግ ከሚያነጋግሩት ርዕሰ ጉዳዮች አንዱ ተጠመቀ የሚባለው «ሰይጣን» ጉዳይ ነው። ዳንኤል ክብረት ይህን ርዕስ አንሥቶ ትክክል ነው በሚለው መንገድ ሐሳቡን ያቀረበው ሲሆን እንዳላየ ያለፋቸው፣ ማብራሪያ ሊሰጥባቸው የሚገቡና አሁንም ጥያቄ የሚያስነሡ ነጥቦች አሉ።

ተጠመቀ ስለሚባለው ሰይጣን ዳንኤል በመጀመሪያ ያሰፈረው «... በገድለ ተክለ ሃይማኖት ላይ አቡነ ተክለ ሃይማኖት አጠመቁት የሚባለው ‹ጋኔን› ጉዳይ በዐሥራ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጥያቄ ሲነሣበት በአዘዘ ተክለ ሃይማኖት የነበረው የዘመኑ ጸሐፊ ‹ጋኔን› ሲባል ምን ማለት እንደ ሆነ በገድሉ ላይ አያሌ ማብራሪያዎችን አክሎበታል» የሚለውን ነው (ገጽ 71)።

ይህም በዚህ ሐሳብ ላይ ጥያቄ መነሣት የጀመረው በዚህ ዘመን ሳይሆን ቀደም ሲልም ጀምሮ መሆኑን ያሳያል። የሚገርመው ጥያቄ መነሣቱ ሳይሆን የአዘዘው ገድለ ተክለ ሃይማኖት ጸሐፊ ለጥያቄዎቹ መልስ ለመስጠት የሞከረው ገድሉ ውስጥ አያሌ ማብራሪያዎችን በማስገባት መሆኑ ነው።

ከዚህ ሐሳብ ወጣ በማለት በዳንኤል መጽሐፍ በልዮ ልዮ ገጾች ውስጥ የሰፈሩትን ሰንመለከት፤

- «በሌሎች ገድሎች የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቀ መዝሙር ከኢጋት ወንዝ አጠገብ አገኘው የሚሉት ‹ሰይጣን› እዚህ (በዋልድባው ገድለ ተክለ ሃይማኖት ማለቱ ነው) ታሪኩ ሌላ ነው። የገዳሙ መነኩሲት[22] ውሃ ልትቀዳ ወንዝ ወርዳ ስትመለስ ታመመች። አቡነ ሃይማኖት ጸሎት ሲያደርጉላት ያሳመማት ‹ሰይጣን› በአምሳለ ወሬዛ ተገለጠ። እርሳቸውም ማን ነህ ከየትስ መጣህ? ሲሉት ‹ሀልወትየስ ኀበ ማይ፣ መሀበ ሀሉ ዕደው› አላቸው። ‹መኖሪያየ ወንዶቹ ከሚገኙበት ከወንዙ ዘንድ ነው› ነው ያለው። ይህ ንግግሩ የባሕር ውስጥ ጋኔን መሆኑን አያሳይም። ‹ተርእየ ዘአድወያ

[22] በብዙዎቹ ገድላት ውስጥ የታመመው ወንድ ሆኖ የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቀ መዛሙር መሆኑ ነው የሚታየው። እዚህ ጋር ግን ታማሚዋ አንዲት መነኩሲት ሆና ተገልጻለች።

በአምሳለ ወሬዛ› ነው የሚለው፡፡ ‹ያሳመማት በኀልማሳ መልከ ታየ›፡፡ ምናልባት በመድኀኒት በአስማት ወይም ደግሞ በልዩ ጥበብ ከሚያፈዙ ሰዎች መካከል ይሆናል፡፡ የመነኩሲቷንም ሕመም ‹ወሰበ ርእያ ቅዱስ እግዚአብሔር ከመ ጠፍዐ ልባ - የእግዚአብሔር ቅዱስም ልቧ እንደጠፋ በተመለከታተት ጊዜ› ይለዋል፡፡ ልብ የመሰወር ሕመም መሆኑን ያሳያል፡፡ ያንን ‹አምሳለ ወሬዛ› አጥምቀው ዘኅረዮ ክርስቶስ ብለው ክርስቲያን አደረጉት›› (ገጽ 96-97)፡፡

ዳንኤል በዚህ ነጥብ ላይ ያሳመማትን አካል ‹ሰይጣን› በሚል ያስቀመጠው ቢሆንም ‹‹በመድኀኒት በአስማት ወይም ደግሞ በልዩ ጥበብ ከሚያፈዙ ሰዎች መካከል ይሆናል›› በማለት እውነታውን ለመሸፋፈን ሲሞክር ይታያል፡፡ ከዚህ ነጥብ ብቻ ‹‹ያሳመማት ‹ሰይጣን› በአምሳለ ወሬዛ ተገለጠ፣ በኀልማሳ መልከ ታየ›› የሚለውን በማንሣት ‹‹በልዩ ጥበብ ከሚያፈዙ ሰዎች መካከል›› ከሆነ በኀልማሳ መልከ ታየ ማለቱ ለምንድን ነው የሚል? ጥያቄ ማንሣት ይቻላል፡፡ ኀልማሳም ይሁን ኅረምሳ ቀድሞም ሰው ነውና ለሁሉ የሚታይ *ሥጋ* ለባሽ በመሆኑ ‹መገለጥ› አያስፈልገውም፡፡

- ‹‹ ‹ሰይጣኑን› *ሥጋ* ለበስ ጋኔን ብሎ መጥራቱ (የሐይቁን ገድለ ተክለ ሃይማኖት ነው) ገድሉ ሁለተኛ/ሦስተኛ ትውልድ መሆኑን ያሳያል፡፡ የመጀመሪያዎቹ ‹ባሪያ› ነው የሚሉት፡፡ የተያዘው ሰው ወንድ ነው፡፡ የተያዘበትም ቦታ ኢጋት የተባለ ወንዝ ነው፡፡ ወደ ቅዱሱም ሲመጣ እንደ ጥቁር ሰው መስሎ ነበር›› (ገጽ 108 እና 145)፡፡

ቀደም ሲል ከሰፈረው ሐሳብ *ጋር* ተስማሚ በሆነ ሁኔታ ሰይጣን መሆኑን ላለመቀበል በትእምርተ ጥቅስ ውስጥ ያስገባውና *ሥጋ* ለበስ *ጋኔን* ነው የሚል መሸፋፈኛ ያበጅለታል፡፡ ግን ደግሞ ‹‹እንደ ጥቁር ሰው መስሎ›› እንደ መጣ የሚናገረው ሐሳቡ መንፈስ እንጂ *ሥጋ* ለበስ አካል እንዳልሆነ ያሳያል፡፡

- ከዚህ በታች የሰፈረው ሐሳብ ከገጽ 615-621 ካለውና ዳንኤል ከልዩ ልዩ ገድሎች ያገኘውን ሐሳብ ገድሎቹን በመጠቁም ካሰፈረው ውስጥ በመውሰዱ ነው፡፡ ሐሳቡን ሙሉ በሙሉ ማስፈሩ 6 ገጽ ሙሉ ጽሑፍ መገልበጥ ግድ ይላል፡፡ በመሆኑም ለዚህ ሐሳብ ተስማሚ የሆኑትን ብቻ መምረጡ ላይ ትኩረት ተደርጓል፡፡
  - ‹‹በሸዋ ምድር ሲመላለስ[23] ሳለ አንድ ቀን በወንዝ አጠገብ ተቀመጠ፡፡ [ከእርሱም *ጋር* ልጁ አብሮ ነበር][24] ልጁንም ባሪያ ያዘውና አሳመመው፡፡ [ቅዱሱም በእጁ ያዘው] በመስቀል ምልክትም አማተበበት፡፡ ወዲያው ወጥቶ መሮጥ ጀመረ ወደ ባሕርም ውስጥ ገባ፡፡ ማር ተክለ ሃይማኖትም ተመለከተውና በባሕሩ ውስጥ ቆሞ ‹የእግዚአብሔር ቁጣ በአንተ ላይ እንዳይወርድ ከባሕሩ ውጣ› አለው፡፡ ያን ጊዜም ባሪያ ወጣ፡፡ በላዩም ላይ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም

[23] በዚህም ሆነ በሌሎች ቦታዎች ዳንኤል በቀጥታ የገድሉን ሐሳብ ሲያሰፍር አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ‹አንተ› ይላል፡፡ የራሱን ሐሳብ በሚያስቀምጥበት ቦታ ደግሞ ‹አንቱ› የሚለውን ይጽፋል፡፡ የዳንኤልን ሐሳብ በቀጥታ በገለበጥንባቸው ቦታዎች ላይ ‹አንተ› የሚለውንና ‹አንቱ› የሚለውን ያገኛሉ፡፡

[24] በዚህ ሐሳብ ውስጥ ያሉት ቅንፎች ሁሉም ከዳንኤል መጽሐፍ ላይ በሰፈሩት መልኩ የተገለበጡ ናቸው፡፡

አማተበበት፤ በእጁም ያዘው፡፡ ሥራዩም ከሸፈበትና እንደ ሰው ለሁሉ ታየ[25] ቅዱሱም… ‹ስምህ ማነው?› ብሎ ጠየቀው፡፡ ባሪያም ‹ባሕር አልቀም› አለ፡፡ ከዚህም በኋላ ገዘረው፡፡[26] ወደ ክርስትናም መለሰው…» (ገጽ 615)፡፡

በዚህ ቦታ ደግሞ ሰይጣን የሚለው ባሪያ በሚለው ስለተቀመጠለት በትእምርተ ጥቅስ ውስጥ ማስገባት አላስፈለገውም፡፡ ነገር ግን «ወዲያው ወጥቶ መሮጥ ጀመረ ወደ ባሕርም ውስጥ ገባ» የሚለው ላይ «ወጥቶ መሮጥ ጀመረ» የሚለውን ስንመለከተው ከምን ውስጥ «ወጥቶ»? የሚል ጥያቄ ማጫሩ አይቀርም፡፡ ለዚህም ቀደም ሲል «[ቅዱሱም በእጁ ያዘው] በመስቀል ምልክትም አማተበበት» በሚል የቀረበው ፍንጭ ይሰጠናል፡፡ ሲማተብበት ሊወጣ የሚችለው መንፈስ ካለሆነ ለሰው ልጅ ወጣ የሚለው ከምን ውስጥ ወጥቶ ነው ወደ ባሕር ውስጥ የገባው ያስብላል፡፡ «ርኵሳን መናፍስቱም ወጥተው ወደ እሪያዎቹ ገቡ» ከሚለውስ በምን ይለያል (ማርቆስ 5÷13)? ከዚህም ሌላ በዚህ ነጥብ ውስጥ «ሥራዩም ከሸፈበትና <u>እንደ ሰው ለሁሉ ታየ</u> ቅዱሱም… ‹ስምህ ማነው?› ብሎ ጠየቀው» በሚለው ላይ ሰወ አለመሆኑን ለመረዳት ይቻላል፡፡

- «ዳግመኛም… አንዲት መነኩሲት እንደ ታመመች ደቀ መዘሙርቱ ለአባታችን ነገሩት፡፡[27]… ሲያጠምቋትም ያሳመማት ነገር በጎልማሳ አምሳል ሲንቀጠቀጥ ታየ፡፡ አባታችንም ‹አንተ ከየት ነህ? በምን ሥራህስ የክርስቶስን አገልጋይ አሳመምኸት?› አለው፡፡… መኖሪያዬስ ወንዶቹ ወዳሉበት ወደ ወንዙ ገደማ ነው፡፡ ልጅህን ውሃ ስትቀዳ በተመለከትኳት ጊዜ ያን ጊዜ ያዝኳት፤ በእርሷ ላይ የምሰለጥን መስሎኝ ነበርና፡፡ ነገር ግን ስመ ክርስቶስን እየጠራህ በእርሷ ላይ በማተብህ ጊዜ የስሙ

---

[25] ዳንኤል እዚህ ጋር በግርጌ ማስታወሻ «የዳጋውና የፓሪሱ (2ኛ) ቅጅዎች ‹ወተከሥተ ለኩሎ እንዘ ይትነባእ ዘነበረ - ተሠውሮ ይኖርበት ከነበረበት (ወጥቶ) ለሁሉ ግልጥ ሆኖ ታየ› ይላሉ» የሚል ነገር ይጨመራል (ግርጌ ማስታወሻ 1805 ይመልከቱ)፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ሰይጣን (ባሪያ) የተባለው አካል መሰወርና መገለጽ የሚችል ነው ማለት ነው፡፡ ይህም መንፈስ የሆነ አካል መሆኑን ያሳየናል፡፡

[26] በገድሉ ውስጥ ከጥምቀት ጎን ለጎን የሠፈረው ግዝረትም ነው፡፡ የገድሉ ጸሐፊ ወይም የድርጊቱ ፈጻሚ ሁለቱን ነገሮች (ጥምቀትንና ግዝረትን) ጎን ለጎን ያደረገበት ምክንያት ግልጽ አይደለም፡፡ ምንም እንኳ በአንዳንድ ቦታዎች «ገርዞም አጠመቀው» የሚል ነገር ቢጻፍም (ገጽ 1014 እና 1031) በገጽ 619 እና 804 ላይ ጥምቀት ሳይኖር «አባታችን ቅዱስ ተክለ ሃይማኖትም ወሰደውና ገዘረው ወደ ታላቅ ክርስቲያንም አስገባው»፤ «ያን ጊዜም ገዘረውና ወደ ታላቁ ክርስትና አስገባው» በማለት ክርስቲያን ለመሆን ግዝረት የሚያስፈልግ መሆኑን በሚያሳይ፤ ከዚህ አለፍ ሲልም ማጥመቅ በማይቻልበት ጊዜ ወይም ቦታ ግዝረትን እንደ ጥምቀት መጠቀም ይቻላል የሚል ሐሳብ ያለው ድርጊት ሲጠቀም ይታያል፡፡ በቤተ ክርስቲያን ትምህርት ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ ነው የሚል ነገር ቢኖርም ሁለቱም ተለዋዋጭ ሆነው (ማጥመቅ በማይቻልበት በመግረዝ፣ ማጥመቅ ሲቻል በማጥመቅ በሚል) አያገለገሉም፡፡ በገድሉ ላይ በዚህ መልኩ የሰፈረው ለምን ይሆን?

[27] በብዙዎቹ ገድላት መሠረት የሚታመመው ወንድ (ከአቡነ ተክለ ሃይማኖት ደቀ መዛሙርት መካከል አንዱ) ሲሆን የሚያሳምመውም ሰይጣን የሚይዘው እርሳቸው ባሉበት ነው፡፡ በዚህኛው ገድል መሠረት ግን ታማሚዋ ሴት ስትሆን በቦታውም እርሳቸው ስለሌሉ ደቀ መዛሙርት መጥተው ለእርሳቸው መንገራቸው ይታያል፡፡

ኃይል ገፋኝ፡፡ ከእርሷም ለየኝ፡፡ እንደ ሰምም አቀለጠኝ፡፡ ልቤም ጠፋ ...» (ገጽ 616)፡፡

በዚህኛ ነጥብ ላይ ብዙ ማብራሪያ ሳይሰጥ «በጎልማሳ አምሳል... ያን ጊዜ ያዝኳት፤ በእርሷ ላይ የምሰለጥን መስሎኝ ነበርና... የስሙ ኃይል ገፋኝ፡፡ ከእርሷም ለየኝ፡፡ እንደ ሰምም አቀለጠኝ፡፡ ልቤም ጠፋ...» የሚሉትን ሐሳቦች ማስቀመጡ ብቻ ሐሳቡን ይገልጠዋል ተብሎ ተሰፋ ይደረጋል፡፡ እነዚህ ቃላት እና ሐረጎች ለሥጋ ለባሽ ሊነገሩ የማይችሉ ናቸውና፡፡

- «...ደቀ መዝሙሩ ታመመ፡፡ የመታመሙም ምክንያት ኢጋት ከሚሏት ወንዝ ሥጋ ለበስ ጋኔን ወጣና ልጁን አሳመመው፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ይህን ዐወቀ፡፡... ያም ጋኔን እንደ ጥቁር ሰው ሆኖ ቅዱሱ ወዳለበት ወጣ...» (ገጽ 617)፡፡

ከላይ እንደቀረበው ያለውን ሐሳብ «ያም ጋኔን እንደ ጥቁር ሰው ሆኖ ቅዱሱ ወዳለበት ወጣ» በሚል መንገድ በዚህም ነጥብ ውስጥ እናገኛለን፡፡ በዚህ ላይ ደግሞ «ጋኔን» መሆኑና «እንደ ጥቁር ሰው» መታየቱ በግልጽ ሰፍሯል፡፡

- «... በውሃ ውስጥ ከሚኖሩ ሥጋ ለበስ ኢጋንንት መካከል አንድ ጋኔን መጣ፡፡ ልጁንም አሳመመው፡፡ አባታችን ተክለ ሃይማኖትም... በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እንዲወጣ አዘዘው፡፡ ያም ጋኔን በጥቁር አገልጋይ ሰው አምሳል ቅዱስ ተክለ ሃይማኖት ወዳለበት መጣ...» (ገጽ 617)፡፡

ይሄኛውም በአገላለጽ ካልሆነ በቀር ከላይኛው ነጥብ ጋር ተመሳሳይ ሐሳብ ነው ያለው፡፡

- «... ተሰውሮ የነበረውም ለሁሉ ተገለጠ...» (ገጽ 618)፡፡

በዚህ አጭር ምንባብ ውስጥ የሚሰወርና በወደደ ጊዜ ደግሞ ለሁሉ መታየት የሚችል አካል ሆኖ ይታያል፡፡ እንዲህ ያለው ነገር ለሥጋ ለባሽ ሳይሆን ለመናፍስቱ የሚነገር ነው፡፡

- «... ጋኔን ወጣና የቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ደቀ መዝሙር ያዘው፡፡ በብርቱም አሳመመው፡፡ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ጋኔን እንደሆነ ዐወቀ፡፡ ‹በጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ርኩስ መንፈስ ከልጄ ዘንድ ውጣ› እያለ በመስቀል አምሳያም በደቀ መዝሙሩ ላይ አማተበ፡፡ ጋኔኑም እርሱን ትቶት ፈጥኖ ሸሸ፡፡... ቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ሄደና ያዘው፡፡ ያን ጊዜም መድኀኒቱ ከሸፈ፡፡ ለሁሉም ታየ ተገለጠ...» (ገጽ 618)፡፡

በዚህ ነጥብ ላይ ከሁሉ በተሸለ ሁኔታ «ጋኔን» መሆኑ «... ጋኔን ወጣና...»፣ «... ጋኔን እንደ ሆነ ዐወቀ...»፣ «... ጋኔኑም እርሱን ትቶት ፈጥኖ ሸሸ...» በሚሉት፤ «ርኩስ መንፈስ» መሆኑም አቡነ ተክለ ሃይማኖት «... ርኩስ መንፈስ ከልጄ ዘንድ ውጣ...» አሉት ተብሎ በተጻፈው የሚታይ ሥጋ ለባሽ አለመሆኑ «... ለሁሉም ታየ ተገለጠ...» በሚል በሰፈረው መረዳት ይቻላል፡፡

- «የዋልድባው ቅጅ ‹በጎልማሳ አምሳል ታየ› ይላል፡፡... የሐይቁና የጣና ቂርቆሱ ቅጅዎች ‹ሥጋ ለበስ ጋኔን› ሲሉት፤ የደብረ ሊባኖሱ ቅጅና ልደተ አበው ‹ጋኔን› ይሉታል፡፡ ገድለ አቡነ አኖሬዎስ ደግሞ ‹ጥቁር ጋኔን› ይለዋል፡፡ ገድለ ተክለ ሃይማኖት ዘቤተ ማረያም፣ ገድለ ተክለ ሃይማኖት ዘአፋፍ ወይራ ማርም፣ ገድለ ተክለ ሃይማኖት ዘደበረ ሊባኖስ፣ ገድለ ተክለ ሃይማኖት ዘጀር ሥላሴ፣ ገድለ

ተከለ ሃይማኖት ዘፍርኩታ ኪዳነ ምሕረት፣ ገድለ ተክለ ሃይማኖት ዘነሐ ጽን፣ ገድለ ተክለ ሃይማኖት ዘሸሜ ማርያም ተጠማቂውን ‹ሰይጣን› ወይም ‹ጋኔን›...›› ይሉታል (ገጽ 621)።

በዚህ ላይ የሰፈሩት ልዩ ልዩ ቅጂዎች ደግሞ «ጋኔን» የሚለውን ለሦስት ጊዜ ያህል ሲያሳዩ «ሰይጣን» የሚለውን ደግሞ አንድ ጊዜ አስፈረውታል። ከዚህም ሌላ «በጎልማሳ አምሳል ታየ» በማለት ሰው አለመሆኑን ፍነጭ ሰጥተዋል። ቅዱሳን መላእክት ሰወ ባይሆኑም በሰው አምሳል መገለጣቸውን መጽፍ ቀዱስ እንደሚያስተምረው ሁሉ ዳንኤልም ሰይጣን በሰው አምሳል የሚገለጥ መሆኑን በዚሁ መጽሐፉ አስፈሯል (ገጽ 527)።

በተመሳሳይ ሁኔታ በሌላ ቦታም «ልደተ አበው ዘደብረ ሊባኖስ» ላይ ያገኘውን፣ «የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ታሪክ፣ የኢትዮጵያ መጻሕፍት እንደሚነገሩን» እና «ገድለ ተክለ ሃይማኖት፤ እንደ አልሜዳ አተራረክ» በሚል ባሰፈራቸው አርዕስት ውስጥ፤

> ከዚህም በኋላ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በየሀገሩ ሲዘዋወር አንድ ቀን በወንዝ ዳር እያለ <u>አንድ ጋኔን</u> ከወንዝ ወጣና ደቀ መዘሙሩን ያዘው፤ አሳመመውም። <u>ጋኔን እንደ ሆነ አውቆ</u> በመስቀል ምልክት አማተበበት። <u>ጋኔኑም ፈጥኖ ወጣ፤ ሸሸም</u>። አቡነ ተክለ ሃይማኖትም በእጁ ያዘው፤ <u>ያን ጊዜም ሥራዩ ከሸፈበትና ለሁሉም ሰው ተገለጠ</u>...።

> ... ከአንደኛው ደቀ መዝሙሩም ጋር በወንዝ ዳር ሲያልፍ <u>ሰይጣን</u> ከወንዙ ውስጥ ወጥቶ ደቀ መዝሙሩን ታገለው። አባታችንም በመስቀል አማትቦ <u>‹ክፉ መንፈስ ከልጂ ውጣ›</u> አለው። እርሱም ትቶት ሄደና ወደ ወንዙ ውስጥ ሊገባ ሞከረ። ቅዱሱ ሲያማትብበት ግን ከወንዙ ዳር ቆመ። ሊዘልልም አልተቻለውም። አባታችንም ተጠጋና ‹ልጂን ለምን ትይዘዋለህ? ስምህስ ማን ይባላል?› አለው። እርሱም ‹እኔስ እንደ ሌሎች ሰዎች መስለኸኝ ነበር። ስሜም ባሕረ አ[ል]ቅም ይባላል› አለው...።

> ... ከዚያም በኋላ ከደቀ መዝሙሩ ጋር ሲሄድ አላነአ ወደሚባል ወንዝ ደረሰ። ከዚያም <u>አንድ ክፉ መንፈስ</u> ወጥቶ ደቀ መዝሙሩን ተገዳደረው። ተክለ ሃይማኖትም በመስቀል አማተበበት። ‹<u>አንተ ክፉ መንፈስ ልጂን ልቀቅ</u>› አለው...

የሚለውን አስነበቧል (ገጽ 804፡ 1014 እና 1031 - አጽንዖት የግል)። በዚህ ሐሳብም ውስጥ ተጠመቀ የሚባለው «ሰይጣን» በርግጥም ሰይጣን (እንደ ዳንኤል አጻጻፍ «ጋኔን») እንጂ ሰው አለመሆኑን «አንድ ጋኔን»፣ «ጋኔን እንደ ሆነ አውቆ»፣ «ለሁሉም ሰው ተገለጠ»፣ «ሰይጣን»፣ «ክፉ መንፈስ» በሚሉት ምንባባት መረዳት ይቻላል።

በራሱ እጅ የተጻፉ እነዚህ ሁሉ እያሉ ዳንኤል ሐሳቡን ላለመቀበል[28] ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። ሐሳቡንም ያቀረበው «ክርስቶስ ጎረዮ የተባለው መነኮስ ሰው እንጂ መንፈስ ሊሆን…» አይችልም በማለት ነው።

«ቅዱሳት መጻሕፍት ከፉዎችን የሰው ልጆች ሰይጣናት ብለው መጥራት ልማዳቸው ነው» የሚለውን ያሰፈረው ዳንኤል ከሚያቀርባቸው የክርክር ሐሳቦች መካከል አንዱ «ሥጋ ለበስ ኢጋንንት መኖራቸውን ከቀድሞ ዘመን ጀምሮ ይታመን ነበር» (ገጽ 626) በማለት ሲሆን ለሐሳቡም ድጋፍ እንዲሆነው ድርሳነ ሚካኤልን ይጠራል።

ድርሳነ ሚካኤልም «በውሃ ውስጥና በየብስ የሚኖሩ ሥጋ ያላቸው ኢጋንንትም አሉ። እነሱ ግን ይጋባሉ ይዋለዳሉ። ዳግመኛም ይሞታሉ» በሚል ይገልጻቸዋል።[29]

ድርሳነ ሚካኤልም ሆነ ዳንኤል ክብረት መሳሳታቸውን የምንረዳው መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢጋንንት በጻፈበት ስፍራ ያሰፈረው ከእነርሱ ሐሳብ የተለየ መሆኑን ስንመለከት ነው። ከዚያ በፊት ግን አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ «ጋኔን» ለሚለው የሰጡትን ትርጉም ማቅረቡ ተገቢ ነው፤

> ጋኔን (ኢጋንንት)፤ በቁሙ መንፈስ ርኩስ ዲያብሎስ፣ የዲያብሎስ ጭፍራ፣ ክፉ ጨካኝ ዕቡይ የሚያሳብድ፤ ከባሕር ከገደል የሚሰድ፣ ከምድር የሚፈጭ የሚያንቁጨቀጭ፣ ከእሳት የሚጥል የሚያንከባልል፤፣ የሚያስፈጥጥና የሚያስገጥጥ፣ የሚያንቅ የሚያሰጨነቅ፣ እንደንጨት የሚያደርቅ።[30]

አለቃ ኪዳነ ወልድ ባሰፈሩት መሠረት ጋኔን (ኢጋንንት) የርኩስ መንፈስ ስም ነው። ይህም መንፈስ (ርኩሳን መናፍስት[31]) መሆኑን ያሳየናል። በመጽሐፍ ቅዱስም[32] ጋኔን

---

[28] ተጠመቆም ሆነ ተገዝሮ ወይም በሁለቱም ክርስቲያን ከሆነ በኋላ ወደ ገነት የገባው ሰይጣን ነው የሚለውን መቀበል ቢቸግረው አይገርምም። ይህን ከተቀበለ ከሁለት ነገሮች አንዱን መወሰን አለበት። (1) ሰይጣን የእግዚአብሔርን መንግሥት አይወርስም ስለዚህ ገድለ ተክለ ሃይማኖት እንዲህ ያለውን ታሪክ በማስፈሩ ተሳስቷል ማለት አለበት፣ (2) ሰይጣኑ ገነትን ወርሷል ሌሎችም ሰይጣናት ንስሐ ለመግባት ከታደሉ ገነትን መውረስ ይችላሉ ብሎ ማመን አለበት። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ገሃነም አስፈላጊነት ሲናገር፤ «ለሰይጣንና ለመላእክቱ ወደ ተዘጋጀ ወደ ዘላለም እሳት ከእኔ ሂዱ» የሚለውን ያሰፈረው ንስሐ የማይገቡና ለገነት የማይበቁ በመሆናቸው ነው። ቤተ ክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ አካል ይሁኑ ከምትላቸው መጻሕፍት መካከል የሆነው መጽሐፈ መቃብያንም «የሚጠፉ በእኔም የሚስቱ ሰዎች ፈጽመው ይበዙ ዘንድ፣ የአዳምም ልጆች ከእኔ ጋር ይጠፉ ዘንድ ይህን በተናገሩ ጊዜ እኔ ደስ ይለኛል፣… ያሳትኋቸው ሰዎች ከእኔ ጋር በእሳት ውስጥ ይጨመሩ ዘንድ ከፈጠረኝ ከእግዚአብሔር ቃል ኪዳን አለኝ።… እስከ ዘለዓለሙ ድረስ ለአንተና በአንተ ለሳቱ ከገሃነም ቅጣት መውጫ የላቸሁም። ነገር ግን ለዘለዓለም በእሳት ውስጥ ትሠቃያላችሁ» በማለት ሰይጣን ጨርሶ ተስፋ የሌለው መሆኑን ያሳያል (3ኛ መቃብያን 1፥15-24 - አጽንዖት የግል)።

[29] ሊቃውንት ጉባኤ፣ ድርሳነ ሚካኤል - በግእዝና በአማርኛ (1989) ገጽ 127።

[30] ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ዐዲስ (1948) ገጽ 324።

[31] የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ *የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት* (1998 - ስምንተኛ ዕትም) ገጽ 243።

ስላደረበት ሰው (ማቴዎስ 12÷22)፣ አጋንንት ያደሩባቸውን ሰዎች (4÷24[33]፤ 8÷16)፣ አጋንንቱ ከሰው ወጥተው ወደ እርያ የሚገቡ መሆናቸውን (8÷31-32)፣ ገብተውበት ከነበረው ሰው ሊወጡ የሚችሉ መሆናቸውን (10÷8፤ 12÷27)፣ በሰው ውስጥ ገብተው የሚኖሩ መሆናቸውን (12÷45) ያሳያል። በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት አጋንንት ሥጋ ለበስ ሳይሆኑ በሰው ሥጋ የሚያድሩ ርኩሳን መናፍስት መሆናቸውን ነው የምናየው። በመጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ስፍራ ላይ ሥጋ ለበስ አጋንንት መኖራቸውን ማግኘት የማይቻል በመሆኑ ዳንኤል ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ ድርሳነ ሚካኤልን ለመጥቀስ ተገዷል።

ማጠቃለያ

ዳንኤል ክብረት ከብዙ ድካም በኋላ ስላበረከተልን ስለዚህ መጽሐፍ እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። እኛ በልዩ ልዩ መንገዶች ስናቀርባቸው የነበሩትን ሐሳቦች ዳንኤል በዚህ መንገድ ለማቅረብ በመጨከኑም ደስ ብሎናል።

ከዳንኤል መጽሐፍ ላይ ለመመልከት እንደሞክረነው ገድላት ከታሪክም ሆነ ከመንፈሳዊ ምክር አንጻር ልባችንን ጥለን ልንደገፋቸው የማንችላቸው ናቸው። ለዚህም ደግሞ ደስ ያለው እየተነሣ የወደደውን የሚጨምርባቸው አልያም የሚሰርዝባቸው መሆናቸው ቀርቧል። ይህ ሥራ ሲሠራ የነበረው ደግሞ በቤተ ክርስቲያኒቱ በራሷ (በገዳማቷና የገድላቱ ባለቤቶች በሆኑት «በገልበጮች») በመሆኑ ሆነ ተብሎ የተደረገ መሆኑን ያሳያል።

በመሆኑም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ለመንፈሳዊ ምክር ልንታመንበት የምንችለው መጽሐፍ የለም ማለት ነው። ስለዚህ የትኛውም ብልህ አንባቢ «ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ

---

[32] ለዚህ ሐሳብ ማሳያ እንዲሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ ከልዩ ልዩ ቦታዎች ጥቅሶችን ከማቅረብ ይልቅ ከአንድ ወንጌል (ከማቴዎስ ወንጌል) ብቻ ማቅረቡ በቂ ሆኖ የተገኘ በመሆኑ ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ከፍሎችን አልተጠቀምንም። አንባቢው ግን በራሱ ጥናት ቢያደርግ በዚህ ጽሑፍ ላይ ከቀረበው የተሻለ ግንዛቤ እንደሚያገኝ ይታመናል።

[33] ድርሳነ ሚካኤል ላይ «ሥጋ ያላቸው አጋንንትም አሉ» የሚለውን ባሰፈረበት ሰፍራ «እነሱ ግን ያ[ሳም]ማሉ እንጂ ማንንም አያስቱም፤ አይገድሉም (ምንም እንኳ ድርሳነ ሚካኤል «እነሱ... አይገድሉም» ቢልም የእርሱ ወንድም የሆነው መጽሐፈ ጦቢት «... አስማንድዮስ የሚባል ክፉ ጋኔን ገድሏቸዋልና» በማለት ኧረ የምን ማሳመም ብቻ መገደልም አለ ይላል)» በማለት የበሽታ ምንጭ መሆናቸውን ይገልጻል ። አያይዞም «በዚህ ዓለም ያለነሱ ደዌ የለም» ይላል። በማቴዎስ 4፡24 ላይ «ዝናውም ወደ ሶርያ ሁሉ ወጣ፤ በልዩ ልዩ ደዌና ሥቃይም ተይዘው የታመሙትን ሁሉ አጋንንትም ያደሩባቸውን በጨረቃም የሚነሣባቸውን ሽባዎችንም ወደ እርሱ አመጡ፥ ፈወሳቸውም» በሚለው ምንባብ ውስጥ ሁለቱም (በሽታም አጋንንትም) ተገልጸዋል። ነገር ግን አጋንንቱ የበሽታ ምንጭ መሆናቸውን አያሳይም። ከዚያ ይልቅ ሁለቱም የተለያዩ ችግሮች እንደሆኑ ነው የሚያታየው። ይህ ማለት ግን በአጋንንት ምክንያት ሰው አይታመምም ማለት አይደለም። በሽታ ሁሉ ከአጋንንት ነው ለማለት «በዚህ ዓለም ያለነሱ ደዌ የለም» በሚል የሰፈረው ሐሳብ ትክክል አይደለም ለማለት እንጂ።

የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ» ከወደደ «ለትምህርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር» ይጠቅማል ተብሎ ወደተመሰከረለት ቃለ እግዚአበሔር ፊቱን መመለስ ይገበዋል (2ኛ ጢሞቴዎስ 3÷16-17)።

ዋቢ

ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፣ (2005 ዓመተ ምሕረት - ሦስተኛ ዕትም) ከሣቴ ብርሃን ተሰማ ዐማርኛ መዝገበ ቃላት። የታተመበት ቦታ እና ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

ተስፋ ሚካኤል ታከለ (መምህር) (ትርጉም)፣ (2002 ዓመተ ምሕረት) ገድለ አዳም። ዐዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤት ያልተጠቀሰ።

ቴዎድሮስ ደመላሽ፣ (መጋቢት 2011 ዓመተ ምሕረት) አታስቀኑት። ዐዲስ አበባ። ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ።

ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ (1989 ዓመተ ምሕረት)፣ ድርሳነ ሚካኤል። ዐዲስ አበባ።

_____፣ (1988 ዓመተ ምሕረት)፣ መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት። ዐዲስ አበባ።

_____፣ (ነሐሴ 1989 ዓመተ ምሕረት)። ገድለ ተክለ ሃይማኖት። ዐዲስ አበባ።

ኪዳነ ወልድ ክፍሌ (አለቃ)፣ (1948 ዓመተ ምሕረት)፣ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ዐዲስ። አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ (1998 ዓመተ ምሕረት)፣ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት። ዐዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት።

_____፣ (2000 ዓመተ ምሕረት)፣ ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ ለኢትዮጵያ አርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የታተመ። ማተሚያ ቤቱ ያልተጠቀሰ።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፣ (የካቲት 1993 ዓመተ ምሕረት)፣ ኣማርኛ መዝገበ ቃላት። ዐዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት።

ዳንኤል ክብረት (ዲያቆን)፣ (ኅዳር 2011 ዓመተ ምሕረት)፣ ኢትዮጵያዊው ሱራፌ። ዐዲስ አበባ፣ ጎትመት ፋር ኢስት ትሬዲንግ ኃላ. የተ. የግ. ማኅበር።

ገብረ ዮሐንስ ገብረ ማርያም፣ (ነሐሴ 1991 ዓመተ ምሕረት)። ክርስትና በኢትዮጵያ - ክፍል ሁለት የታተመበት ቦታ እና ማተሚያ ቤቱ ያልተገለጸ።